





# ፲፯



**አሸናፊ ከበደ**

**1931 –1991**

**ውስጥ አዘንባይ ነፍስ አባባይ**

**[ሙዚቃ] የብቻ ጕዞ ነው፤ በራስህ እንደ ደረስህበትና እንደ ገባህ ማቀናበር ነው። ስለዚህ ለማንም ስለምትሠራው ነገር [ሙሉ በሙሉ] መናገር አትችልም። በዚህም ምክንያት ለብቻዬ እሠራለሁ፤ የራሴን የማቀናበር ስልትም እከተላለሁ**

ወቅቱ እ.ኤ.አ 1967 ዓ.ም. ነው። በቡዳፔስት ሃንጋሪ ታላላቅ አውሮፓውያን የሙዚቃ አቀናባሪዎች የሙዚቃ ሥራዎቻቸውን ባቀረቡበት አዳራሽ ውስጥ አንድ አዲስ ክሥተት ታየ። ይኸውም በዚያ የነበረውን የአውሮፓ የሙዚቃ ኦርኬስትራ ለመምራት ቆሞ የነበረው ከአህጉረ አፍሪካ የ26 ዓመቱ ኢትዮጵያዊ ወጣት አሸናፊ ከበደ መሆኑ ነው። ይህ ወጣት የሙዚቃ አቀናባሪ በሚያስደንቅ ሁኔታ ቅንብሩን ከመምራቱ የተነሣ በጊዜውና በቦታው የነበሩት ነጭ ተመልካቾች፦ «አንድ ጥቁር አፍሪካዊ በሙዚቃ ትምህርት የሠለጠኑትን የነጮች ኦርኬስትራ እንዴት ሊመራ ቻለ?» በማለት አድንቀው ነበር።

የመጀመሪያውንና ታላቅ የሆነውን "እረኛው ባለዋሽንት" የሚለውን ቅንብሩን በይፋ ካቀረበ በኋላ የፕሮፌሰር አሸናፊ ዝና በመላው ሃንጋሪ ናኘ። ሃንጋሪያውያን በአገራቸው ታዋቂ ከነበረውና እ.አ.አ ከ 1882 -1967 ዓ. ም. ከኖረው ዞልታን ኮዳሊ ከተባለው የሙዚቃ አቀናባሪ ጋር በማመሳሰል «ጥቁሩ ኮዳሊ» የሚል ስም ሰጡት። ፕሮፌሰር አሸናፊ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ የዐለም ዓቀፍ የሙዚቃ ትእይንቶች ላይ ተገኝቷል። በተለይም በ1960ዎቹ አካባቢ በርካታ ሙዚቃዎችን አቀናብሯል፤ ብዙ ኦርኬስትራዎችንም መርቷል። በተጨማሪም ስለ ሦስተኛው ዓለም አገሮች፣ ስለ ዐረብ፣ ስለ ጃፓንና ስለ አውሮፖ ሙዚቃ ከነበረው ጥልቅ ዕውቀት የተነሣ በሙዚቃ ጥበብ /ሚዩዚኮሎጂ/ ታላቅ ሰው ለመባል በቅቷል። በዚህም ምክንያት ታላላቅ የሙዚቃ ሰዎችንና ሥራዎቻቸውን ይዘው በሚወጡ ጽሑፎች ላይ ስሙ ተጽፏል። በ*International Who is Who In Music* እንደዚሁም ከአፍሪካውያንና አፍሪካ አሜሪካውያን ታዋቂ ሙዚቀኞች ተርታ ሳይቀር አንዱ ሆኖ ተቈጥሯል።



ፕሮፌሰር አሸናፊ በ 1962 ዓ. ም. አሜሪካን አገር በነበረበት ጊዜ በጆርጅታውን ዩኒቨርስቲ በቋሚ ተቀጣሪነት ወደ ኢትዮጵያ የሚሄዱና ፒስ ኮር በመባል የሚታወቁ የሰላም ልኡካንን አማርኛ ቋንቋ ያስተምር ነበር። በዚያም እያለ አማርኛ



አስተማሪዋ ሆኖ ለመጀመርያ ጊዜ እንዳገኘችውና ከዚያም ሁለቱም ኢትኖሚዩዚኮሎጂ ባለሙያ ስለሆኑና በኢትዮጵያ ላይ የጋራ ርእይ ስለ ነበራቸው ለረጅም ጊዜያት አብረው እንደሠሩ ሲንቲያ ኪምበርሊን የተባለች የሙዚቃ ባለሙያ ገልጻለች። ሲንቲያ፣ በፕሮፌሰር አሸናፊ የኪነ ጥበብና የትምህርት ሕይወት ዙሪያ ጽሑፎችን አበርክታለች።

ፕሮፌሰር አሸናፊ ከሙዚቃ አቀናባሪነቱና ከኤትኖሚዩዚኮሎጂስትነት ባሻገር የፈጠራ ጸሓፊም ነው። ለምሳሌ ፦ ከሥራዎቹ መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀስለትና በ1964 ዓ.ም. የታተመው *'Confession'* የተባለው ድርሰቱ ሐያሲያንን በመማረክ የአፍሪካ ደራስያን ፣ አራቱ የአፍሪካ ሥነ ጽሑፎች */Four African Literatures /* በሚሏቸው ኅትመቶች ውስጥ ተካቶ ሊጻፍ በቅቷል።

ከዚህም ባሻገር የተለያዩ ሥራዎቹን ማለትም ከሙዚቃ ጋር የተያያዙ መጣጥፎችን፣ በዐለም ሙዚቃ ላይ የጻፋቸውን መጽሐፎቹን ጨምሮ ለኅትመት አብቅቷል። ሙዚቃ ነክ ከሆኑት ሥራዎቹ መካከል እ.ኤ.አ በ1966 ዓ. ም. የሙዚቃ ሰዋሰው፣ የአምባራስ የአዝማሪ ሙዚቃ በ1969 ዓ. ም. ፣ የአፍሪካ ሙዚቃ በምዕራቡ ዓለም በ1972 ዓ. ም. ፣ *"The Bowl-Lyre of North East Africa. Kirar: the Devil's instrument"* በ 1977 ዓ ም ሙዚቃ በጥቁር አይሁዶችና በክርስቲያን ማኅበረ ሰብ፣ በ 1980 ዓ. ም. የኢትዮጵያ ዘመናዊና ባህላዊ ሙዚቃ ሂደት፣ በ1976 ዓ. ም. የጥቁሮች ሙዚቃ ሥረ መሠረት፣ የአፍሪካውያንና የጥቁር አሜሪካውያን የሙዚቃ መሣሪያ ዐይነቶችንና ውዝዋዜዎችን የዳሰሰባቸው የጽሑፍ ሥራዎችና የኢትዮጵያ ሙዚቃ ዘመናዊ አባባሎችና ግጥሞችን ለእትመት አብቅቷል። ከ 8 የሚበልጡ ዋና ዋና የሙዚቃ ሥራዎችንም አቀነባብሮ አበርክቷል።



ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ */Senior Fulbright Scholar/* የሚል የምሁርነት ስያሜ የተሰጠው ሲሆን የተለያዩ ሽልማቶችንም አሸናፏል። ለምሳሌ፦ *UNESCO Florida Fine Arts Counsel, Na-*

*tional Endowment for the Humanist, Canada National Music Counsel, American Learned Society Counsel* እንዲሁም *UNESCO Research Grant* ሽልማቶችን ተቀብሏል። ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ በአሜሪካን ፍሎሪዳ ግዛት ዩኒቨርስቲ ውስጥ የአፍሪካ አሜሪካውያን ባህል ማእከል ዲሬክተር፣ የዘክሮኒክለር ጆሔናል ዋና አዘጋጅ እንዲሁም ጥበብን ለሚያስተዋውቅ ኢቲዮስ ለሚባል ዐለም አቀፋዊ ድርጅት ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ለ19 ዓመታት አገልግሏል።

ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ በ 1931 ዓ. ም. በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ። እናቱ ወ/ሮ ፋንታዬ ነከሬ ከቤተ ሰበ ሁሉ የኪነ ጥበብ ሰው ነበሩ። ሃይማኖታዊ ይዘት የነበራቸውን ግጥሞችና ንባቦች እንዲሁም ያሬዳዊ ዜማዎችን ይጽፉ እንደ ነበር፣ በተጨማሪም በዝማሬ መልክ ለቅድስት ማርያም ምስጋና በየቀኑ ያቀርቡና ለእርሱም የዳዊትን መዝሙር በበገና በየምሽቱ ይጫወቱለት እንደ ነበር በመጥቀስ እናቱ በሙዚቃ ጥበብ ሁነኛ ተጽዕኖ እንዳሳደሩበት ያስታውሳል። የፕሮፌሰር አሸናፊ እናት የሞቱት ግን የ9 ዓመት ልጅ እያለ ነው። ከዚህ የተነሣ፣ «አሁን የእኔ ዕድሜ ከኀምሳ ዐመት በላይ ቢሆንም የእናቴን ሞት ልረሳ አልቻልኩም። አሁንም ቢሆን ልቤ እንደ ተሰበረ ነው። ለዚህም ነው ሁልጊዜ ትካዜ ውስጥ አዘንባይ /*Melancholic*/ የሚሆነው» ሲል ባንድ ወቅት ተናግሯል። በርግጥ ለመናገር ሙዚቃዎቹ ከፍተኛ ጥበብን የተላበሱ ሆነው ሐዘንን የሚጭሩ ናቸው። በምሣሌነትም እረኛው ባለ ዋሽንት ሊጠቀስ ይችላል። በሌላ ጎኑ ደግሞ የፕሮፌሰር አሸናፊ ሙዚቃዎች መንፈስን የሚያነቃቁም እንደሆኑ ከብዙዎች እንደበት ይሰማል።

ለሙዚቃ የተለየ ፍቅር ማሳየት የጀመረው ግና በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበረበት ጊዜ ነው። የተወሰኑ የሙዚቃ ኮርሶችን በወሰደበት በሐረር የመምህራን ማሠልጠኛ የሙዚቃ ፍቅሩ በይበልጥ እያደገና እየጨመረ ሔደ። ከሐረር የመምህራን ማሠልጠኛ ከተመረቀ በኋላ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ





ዩኒቨርሲቲና በአዲስ አበባ ወ.ወ.ክ.ማ ሁለት ዓመት አስተማረ። ከዚያም ወደ አሜሪካ በመሄድ በኒውዮርክ ከሚገኘው ከሮችስተር ዩኒቨርስቲ ኢስት ማን ከለብ ኦፍ ሚዩዚክ የመጀመሪያ ዲግሪውን አገኘ። በ 1962 ዓ. ም. ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት ተከፈቶ ስለ ነበር በዚያ ዲሬክተር ሆነ። ወደ አሜሪካ ከመሄዱ በፊትና ከመጣም በኋላ በርካታ መዝሙሮችን ደርሷል። ከድርሰቶቹ መካከልም፣ «ሰላም ኢትዮጵያ» ፣«የመሰላል ጫማ» ፣«የፍቅር ነቀርሳ»፣ «የተማሪ ፍቅር» እና «የአገራችን ሕይወት» የሚባሉት ይገኙበታል።

ፕሮፌሰር አሸናፊ የያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት ዲሬክተር ሲሆን ዕድሜው 25 ነበር። ግና በወጣትነት የእድሜ ክልል የኢትዮጵያን ሙዚቃ ለዓለም ለማስተዋወቅ ከፍተኛ ጉጉት ነበረው። በዚህም የተነሣ የኢትዮጵያ ባህላዊ ዘፋኞችንና የቀሳውስትን ቡድን ይዞ በአውሮፓና በእስያ በመጓዝ «ሙዚቃችንን እናስተዋውቅ» በማለት የትምህርት ሚኒስቴር ለነበሩት ለአቶ አካለ ወርቅ ሀብተወልድ ጥያቄ አቀረበ። ሚኒስትሩ በወቅቱ ሐሳቡን ስላልተረዱለት ለጥያቄው አዎንታዊ ምላሽ ባይሰጡትም፣ በራሱ ኀላፊነት የቡድኑን አባላት ይዞ ወደ ተጠቀሱት አገሮች በመሄድ ውጤታማ የሆነ ሙዚቃችንን የማስተዋወቅ ሥራ ሰርቶ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል። በዚህ ጊዜ ሚኒስትሩ የተገኘውን ውጤት ሰምተው በመደሰት ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ጣቢያ ተገኝተው ለቡድኑ አቀባበል ያደረጉላቸው ሲሆን ከቡድኑ ጋርም የመታሰቢያ ፎቶግራፍ ተነስተዋል።

የፕሮፌሰር አሸናፊ ጥረትና ውጤት ንጉሡ ዘንድ ሲሰማ ወጣቱን አሸናፊ በማድነቅና በሚያዘጋጀው ኮንሰርት ላይም እንደሚገኙ ቃል በመግባት የሚወዱትን «እረኛው ባለ ዋሽንት» የሚለውን የመጀመሪያ አልበሙን እንዲያሳትም በገንዘብ ረዱት። በዚህም ሳያበቃ እ.ኤ.አ በ1967 ዓ. ም. «ብሔራዊ የሙዚቃ አቀናባሪ» በሚል የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ *Foundation Grant for Outstanding Achievement in Cultural Affairs* የመጀመሪያ ወጣት ተሸላሚ ለመሆን በቃቷል።



ንጉሡ ሰባ አምስተኛ የልደት በዓላቸውን ሲያከብሩም፣ የአሸናፊ ሥራዎች በበዓሉ ላይ ለተገኙት ታዳሚዎቻቸው በማስታወሻነት እንዲሰጡ አድርገዋል።

ወጣቱ የሙዚቃ ባለ ሙያ አሸናፊ ከበደ እ.ኤ.አ ከ1963-1968 ዓ. ም. ድረስ በያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት ሲሠራ ከቆየ በኋላ የድኅረ ምረቃ ትምህርቱን ለመከታተል ወደ አገረ አሜሪካ አቀና። እዚያም በ1969 ዓ ም ከዌስሊያን ዩንቨርሲቲ በኤትኖሚዩዚኮሎጂ (ምዕራባዊ ያልሆነ የባሕላዊ ሙዚቃ ጥናት) የማስተር ኦፍ አርትስ ዲግሪውን አገኘ። በመቀጠል ደግሞ በ1971ዓ.ም. ከዚያው ዩንቨርሲቲ በኤትኖሚዩዚኮሎጂ የፒ. ኤች.ዲ. ዲግሪውን የተቀበለ ሲሆን፣ የመመረቂያ ጽሑፉም «የኢትዮጵያ ሙዚቃ እድገት እና ባህላዊ ዳራ» የተሰኘ ነበር። ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ ከ 1970-1976 ዓ. ም. አሜሪካን አገር በኩዊንስ ኮሌጅ በረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ በኤትኖሚዩዚኮሎጂ ፕሮግራም ዲሬክተርነት አገልግሏል።

የፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ ዋና ጥረት የነበረው በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ያሉ አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን የወከለ አንድ ዐይነት የሆነ የሰው ልጆችን ማንነት የሚገልጽ የሙዚቃ ቅንብርን አግኝቶ በእርሱ አማካኝነት ኪነ ጥበብን መግለጽ ነበር። በ20ኛው ክ/ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ላይ በዓለም ውስጥ ለሚታየው የዘር ግጭትና መድሎ እንዲሁም ማኅበራዊ ኢፍትሐዊነት መፍትሔ የሚሆንን ነገር በሙዚቃው ውስጥ ይፈላልግ ነበር።

ፕሮፌሰር አሸናፊ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ከሙዚቃ አቀናባሪነቱ ይልቅ በምሁርነቱና በመምህርነቱ የበለጠ ይታወቃል። በሙዚቃው ቅንብር ከዓለም ዐቀፍ መርሖች ይልቅ በራሱ ፈጠራ ላይ ያተኩራል። ከዚህ



የተነሣም ምዕራባውያን ባስቀመጡት የሙዚቃ ምድብ ሊፈረጅና ደረጃው ሊታወቅ አልቻለም። ለዚህ ነው በአንድ ወቅት፣ ስለ ሙዚቃ ቅንብሩ ሲናገር «የብቻ ጉዞ ነው፤ በራስህ



እንደደረስህበትና እንደ ገባህ ማቀናበር ነው። ስለዚህ ለማንም ስለምትሠራው ነገር መናገር አትችልም። በዚህም ምክንያት ለብቻዬ እሠራለሁ፤ የራሴን የማቀናበር ስልትም እከተላለሁ» በማለት ስለ ራሱ የተናገረው። ሲንቲያ *Ethnomusicology* በተሰኘ አንድ የሙዚቃ ጆርናል ስለ ፕሮፌሰር አሸናፊ የሙዚቃ ቅንብር የብቻ ጉዞ ስትናገር እንዲህ ትላለች፦

> አንድ ጊዜ 1997 (እ.ኤ.አ.) በዓመቱ መጀመሪያ ገደማ ፕሮፌሰር አሸናፊን አገኘሁትና በአማርኛ ያሉትን የሙዚቃ ቅንብሮቹን ጨምሮ ርእስ እንዲሰጠኝና ለሥራ ባልደረቦቼ ላሳያቸው ስል ጠየቅኩት እሱ ግን በአሳዛኝ ሁኔታ፣ ስለ እኔ ሥራ ፍንጭ ለሌላቸው ኮሚቴ መሰሎች በአማርኛ የሥራዎቹን ርእስ ዝርዝር ማቅረብ ትርጉም የለሽ ከመሆኑም በላይ አሰልቺ ይሆናል ሲል መለሰልኝ።

ከኢትዮጲያ ፔንታቶኒክ (ባለ አምስት) ቅኝት ጋር ተመሳሳይ የሙዚቃ ቅኝት ያለውን የጃፖን ሙዚቃ ለአብነት በመውሰድና ሁለቱን በማዋሐድ እንዲሁም የኢትዮጵያን ዜማ ለጃፖን የሙዚቃ መሣሪያ እንዲመች አድርጎ በማቀነባበር ለሁለቱም አገሮች የሙዚቃ እድገት አስተዋፅኦ አበርክቷል። ይህ ጥበባዊ የፈጠራ ግኝቱ ፕሮፌሰር አሸናፊን በጃፖን፣ በኢንዶኔዥያና በህንድ ሙዚቃም ላይ ሊቅ አሰኝቶታል። ይህም ብዙ ቋንቋዎችን እንዲናገር፣ ብዙ ባህሎችንም እንዲያውቅና እንዲያጠና አስችሎታል። ከዚህም በተጨማሪ በኢትዮጵያ የአምባሰል ቅኝትና በጃፖን በራጂሺ ቅኝት መካከል ከፍተኛ ተመሳሳይነት እንዳለ ደርሶበታል።

በተጨማሪም ፕሮፌሰር አሸናፊ የኢትዮጵያ ሙዚቃ በአውሮፖ የሙዚቃ መሣሪያዎች እንዲዳብርም አድርጓል። በጣም የሚወዳቸውን የሙዚቃ መሣሪያዎች፣ ለምሣሌ፦ ዋሽንትን፣ ክላርኔትንና ቫዩሊንን በመጠቀምና የኢትዮጵያን ዜማ በማስገባት አስደናቂ ኢትዮጵያዊ ዜማዎችን ለመፍጠር ችሏል። ለምሣሌ «እረኛው ባለዋሽንት» እና አራቱ ዋና ዋና ሥራዎቹን ጨምሮ ኮቶ ዚተር በሚባል ባለ



13 ክር መሳሪያ ክላርኔት ወይም ፍሉትና ቫዮሊን በመጠቀም የተጫወታቸው ናቸው። ይህ የኢትዮጵያን ዜማ ከምሥራቅና ከምዕራብ የሙዚቃ መሣሪያዎች ጋር በመቀላቀል በሙዚቃ ዓለም ሀቀፋዊነትን የፈጠረ ሲሆን፣ በዚህ ሥራውም ሁለቱንም የዓለም ጎራ ማለትም ምሥራቁንና ምዕራቡን ሊያስደንቅ ችሏል። በዚሁ ሙያ በቆየበት ዘመን ሁሉ ለትውልድ አገሩ ለኢትዮጵያና እንዲሁም ለጃፖን ፣ለመካከለኛው ምሥራቅ ፣ለህንድ ፣ለምሥራቅ አውሮፖ፣ በተለይም ለሀንጋሪና ለዩኤስ ኤ ሙዚቃ የተለየ ትኩረት ነበረው።

ፍሎሪዳ ውስጥ በሚገኘው የታለሀሴ ዩኒቨርስቲ በአፍሪካ አሜሪካ የባህል ማእከል በዳሬክተርነት በቈየበት ጊዜ፣ የአፍሪካንና የአፍሪካ አሜሪካንን ዳንስ፣ ሙዚቃ እና ድራማ በፍሎሪዳ ከተማ እንዲታይ ያደርግ ነበር። ፕሮፌሰር አሸናፊ ከታላቅ የሙዚቃ አቀናባሪነቱም በላይ ልዩ ተሰጥዎ ያለው አስተማሪ ነበር። እርሱ በነበረበት ኮሌጅ ውስጥ የሙዚቃ አስተማሪ የነበረች አንዲት ሴት ስለ ፕሮፌሰር አሸናፊ በተማሪነቷ ጊዜ ስለነበራት ትውስታ ስትናገር፣ «እ.ኤ.አ በ1970ዎቹ ውስጥ ሙዚቃ በሚያስተምረን ወቅት ምርምር ያሠራን ነበር። ከክፍል በፊትና በኋላ የአፍሪካ ሙዚቃ እንሰማለን። ከተዛባ አመለካከታችን የተነሣ ቀድሞ እንጠላው የነበረውን የአፍሪካ ሙዚቃ መውደድ ጀመርን። ከዚህም የተነሣ የጥቁር አፍሪካ፣ የእስያንና የዐረቡ ዓለም ሙዚቃዎች በኮሌጁ የኮርስ ዝርዝር ውስጥ ተካተቱ።» ብላለች።

ፕሮፌሰር አሸናፊ ብዙ ጊዜ በብቸኝነት ወቅት ወደ ራሱ ውስጥ ገብቶ ከነፍሱ ውስጥ ጥልቅ ነገር በማውጣት፣ በሚያቀናብራቸው የሙዚቃ ሥራዎቹ፣ አድማጮቹ በከፍተኛ ተመስጦ ቅንብሩን ማዳመጥ የሚችሉበትን ሁኔታ ይፈጥር ነበር። ምስጢር ዐዘል የሆኑ የአፍሪካና የሩቅ



ምሥራቅ ሀሳቦችንና አባባሎችን በቅንብሩ ውስጥ ከተለያዩ ድምፆች ጋር ይጠቀምና ያካትት ስለ ነበር፣ የሙዚቃ ቅንብሮቹን በሚያሳይበት ወቅት ታዳሚዎቹ አዲስ የሆነ አስደናቂ ምት ፣



ጣዕምና የድምፅ ቅንጅት በቅንብሩ ውስጥ መስማት ይችሉ ነበር።

ፕሮፌሰር አሸናፊ ከሙዚቃ የሥነ ልቡናዊ ፈውስነት ባሕርይ በመነሣት *South West School of Hypnotherapy* በሂፕኖቴራፒ ሰርተፍኬት አግኝቶ በአሜሪካን ሂፕኖቴራፒ ማኀበር ውስጥ በሂፕኖቴራፒስትነት ተመዝግቧል። ከዚህም ሌላ በማህበረ ሰብ ባሕልና በሙዚቃ መካከል ያለውን ግንኙነት /ኤትኖሚዩዚኮሎጂ/ በማጥናቱ፣ ስለ ሰው ልጅ ጥናትም /*Anthropology*/, ሰፊ ዳሰሳ እንዲያደርግ አነሣሥቶታል። የፕሮፌሰር አሸናፊ የሙዚቃ ቅንብሮች ውስጣዊ ስሜትን የሚፈጥሩትን ያህል በውጫዊ ነገሮችም ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ። ለምሣሌ አንዳንድ ቅንብሮቹ በማኅበረ ሰብ፣ በፖለቲካና በመንግሥት ላይ ያተኩሩ ሲሆኑ ከፊሎቹ ደግሞ በቀጥታ ከሙዚቃና የሙዚቃን ቅንብር ከሙተወን ጋር ይያያዛሉ፤ ቀሪዎቹ ደግሞ ከሣይንስና ከቴክኖሎጂ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው። እ.ኤ.አ በ1960ዎቹ እና በ1970ዎቹ በነበሩት የኢትዮጵያ መንግሥታት ጫና የተነሣ የግጥምና የዜማ ይዘቶች ፖለቲካውንና ርእዮተ ዓለሙን በሚደግፉበት መልኩ እንዲደረሱ ይደረግ ነበር። ከነበረው ጫና የተነሣ የፕሮፌሰር አሸናፊ የግጥምና የዜማ ድርሰቶች ውጫዊ ይዘታቸው ባለ ሥልጣናቱ እንደሚፈልጉት ቢመስሉም በውስጣቸው ግን ድብቅ ምስጢርን ያዘሉ እንዲሆኑ አድርጓል። ይህ ጫናም ፕሮፌሰር አሸናፊን አዲስ ወደ ሆነ የሙዚቃ ቅንብር እንዲመጣ ገፋፍቶታል። በተለያዩ የውጭ አገራት መሔዱም የተለያዩ የሙዚቃ አቀናባሪዎችን፣ ሙዚቀኞችንና አያሌ ምሁራንን ለማግኘት አጋጣሚ የፈጠረለት ሲሆን ከእነዚህ ጊዜያት ጀምሮ ምስጢራዊና ድብቅ የሆኑ መልእክቶች በአሸናፊ የመዝሙር ግጥሞች፣ የጽሑፍ ግጥሞችና እንዲሁም በንግግሮቹም ውስጥ በስፋት መታየት ጀመሩ።

ፕሮፌሰር አሸናፊ እ.ኤ.አ አቈጣጠር ግንቦት 8 ቀን 1998 ዓ. ም. በታለሃሴ ፍሎሪዳ ዩኒቨርስቲ በማገልገል ላይ እያለ ከዚህ ዓለም



በሞት ተለየ። ፕሮፌሰር አሸናፊ ከመጀመሪያ ባለቤቱ ከወይዘሮ እሌኒ ገ/መስቀል ኒና አሸናፊና ሡናይት አሸናፊ የሚባሉ ሁለት ሴት ልጆች ወልዷል። ኒና በጠበቃነት የምታገለግል ሲሆን፣ ሁለተኛዋ ልጁ ሡናይት ደግሞ በተዋናይነት ትሠራለች። ፕሮፌሰር አሸናፊ ጥንታዊውን ኢትዮጵያዊ ባለቅኔና የሙዚቃ አቀናባሪ የነበረውን ቅዱስ ያሬድን የሚያደንቅና የሚወድ ከመሆኑ የተነሣ አሜሪካዊ ዜግነት ካላትና ኤትኖሚዩሲኮሎጂስት ከሆነችው ሁለተኛዋ ባለቤቱ ከዶ/ር ሜትኮዊክስ የወለደውን ልጁን ያሬድ ብሎታል ።

## መወድስ

**ነበር ከመባል አልፌሃል**
**ሕያውነትህን በሙዚቃ ቃናህ አብስረሃል**
**አሸናፊ ወደ ውስጥህ አዘንብለህ**
**ምጠህ ተማምጠህ ሕያዊት ሙዚቃ ወልደህ**
**ከነፍስህ ለነፍስ ማባበያ አፍልቀህ**
**በደማቅ አሻራህ ሁሌም ትኖራለህ**





## ትምህርተ ውልብታ

**ተሰጥዎን ያለማቋረጥ ማዳበር ለስኬት ያበቃል።**

**በየሙያ ዘርፋችን የግድ የሌሎችን መንገድ መከተል የለብንም፤ የራሳችን የሆነ የሙያ ስልትና የፈጠራ ችሎታ ልናዳብር ይገባናል።**

**ከተጽእና በላይ መራመድ፣ ተጽእኖን ለማሸነፍም ጥበበኛ መሆን።የወላጆች በጎ ተጽእኖ የልጆችን ዘላቂ የሙያ መስክ ሊወስን ይችላል።**

## የውልብታ ምንጭ


Fikre Tolossa, "*Ashenafi Kebede: A composer with soul,*" Ethiopian Review May, 1993.

Kimberlin, Cynthia Tsekimberlin, "*The scholarship and art of Ashenafi kebede (1938-1998)*", Etnomusicology 43,2, 1999, 322-34

Kimberlin, Cyntain in Ashenafi Kebede, *Enyclopedia Aethiopica*, Harrassowitz verlog

Dale A. Olsen, ww.fsu.edu/fstime/FSTimes/Volume4/aug98




## የአንባቢው የግል ማስታወሻ






# ፲፰



**ጀምበር ተፈራ**

**1935**

**የዘመን ፍልሚያ በድኻ ጉያ**

**"ርእይን ከሚጋራ ሰው ጋር ርእይ ሰጠኝ!"**

ዐይነ ስውሩ አቡሌ ተጠግቶ በሚኖርበት ግቢ ውስጥ የምታስብለትና የምትጨነቅለት አንዲት ሕፃን ልጅ ነበረች። ልጅቷ ጠዋት ጠዋት ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ፣ አቡሌ ከመጽዋቾቹ ጋር ይገናኝ ዘንድ ሰው በብዛት በሚመላለስበት አውራ መንገድ ዳር ታስቀምጠዋለች። ከተማሪ ቤት ስትመለስ ደግሞ ወደ ማደሪያ ጎጆው እየመራች ትወስደዋለች:: ለአቡሌ ይህን ፍቅር ትለግሰው ዘንድ ያባበላት፣ ልቧ ውስጥ የተፈጠረው አዛኝነትና ርኅራኄ እንጂ ከእርሱ ጋር ያላት ዝምድና ወይም ከሌላ አካል የመጣ ትእዛዝ አልነበረም።

ይህቺን ብላቴና አዱኛ (ሀብት) በተሟላበት በእርሷ ቤተ ሰብና በለምኖ አዳሪው በአቡሌ መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት ዘወትር እንድታሰላስልና እንዲሁም "ድኽነት ምንድን ነው?" በማለት ራሷን ደጋግማ እንድትጠይቅ ያደርጋት ነበር። አቡሌ ልጂቱ እየመራችው ጐዳና በመውጣት እጁን ዘርግቶ ምጽዋት ይጠይቅ እንጂ ቀኖች ሁሉ ለእርሱ እኩል የተሳኩ አልነበሩም። በበዓላት ቀናት እጁ በሣንቲም፣ ኮረጆው ደግሞ በእንጀራና በዳቦ ቢሞላም፣ ገብርኤል፣ ማርያምና ሚካኤል በማይውሉባቸው ቀናት ግን እጆቹ ሣንቲም፣ ኮረጆው ፍርፋሪ ይራባሉ። በእነዚህ ቀናትም ልጅቱ ጠጋ ብላ፣ "አቡሌ ዛሬ ቀናህ?" ትለዋለች። አቡሌም ግራ እጁን ልጅቱ ትከሻ ላይ እያደረገ፣ "ዛሬ አልቀናኝም!" ይላታል። የአቡሌ የቀን ሙሉ ልመና ባዶ መሆኑን ስታስብ ልጂት ታዝናለች፤ትተክዛለችም።

አንድ ሐሳብ መጥቶላት ሩጭ ብላ ጠራችው፤ "አቡሌ!" እጇን ወደ ቦርሳዋ ሰድዳ ሣንቲሞች እየፈለገች።

"አቤት ጀምበር!" አለ አቡሌ.

"እንካ!"

"ምን?" አቡሌ ከጥያቄው ጋር እጁን ወደ ፊት ዘረጋ። ቀኑን ሙሉ ደክሞ ያላገኛቸው ሣንቲሞች የእጁን መዳፍ ሞሉት።



"ከየት አመጣሽው?" "እናቴ የሰጠችኝ የኪስ ገንዘብ ነው፤ ያዘው! እኔ ብገዛበት ከረሜላ ነው። ለአንተ ግን ራት መቅመሻ ይሆንሃል።"



አቡሌ በማያየው ዐይኑ ይህቺን ልበ ብርሃንና አስተዋይ ልጅ ያያት መሰለ። በሳል አስተሳሰቧን አእምሮዋ ውስጥ ገብቶ ገመገመው።

"እግዚአብሔር ይስጥሽ! እግዚአብሔር ለፍሬ ያብቃሽ! ወገኖችሽን የምትጠቅሚ ልጅ ሁኚ!" ብሎ መረቃት፤ ለእርሷ መስጠት የሚችለው ምርቃት ብቻ ነበርና።

እናት ከተማሪ ቤት የመጣችውን ልጃቸውን በጨዋታ እየተቀበሏት ነው።

"ጀምበር!" በማለት ተጣሩ

"አቤት!"

"የሰጠሁሽን የኪስ ሣንቲም ምን አደረግሽበት;"

"ዛሬ አቡሌ አልቀናውም ነበርና ለእርሱ ሰጠሁት።"

እናት ዕድሜዋን ቀድማ የበሰለች ልጃቸውን አተኩረው እያዩ፣ "ጎሽ የኔ ልጅ! ደግ አድርገሻል! እንኳን ሰጠሽው" አሏት። ልጅቱም "ለካ ከረሜላ ከመብላት ይልቅ ለአቡሌ ሣንቲም መስጠት ያስመስግናል!" ስትል አወራች ከራሷ ጋር። አውርታም አልቀረችም፤ የድኾች አለኝታ እንደ ሆነች በዚሁ ገፋችበት እንጂ።

ጀምበር አሥር ዓመቷ ገደማ ላይ ከድኾች ጋር አብራ እንድትሠራ ምክንያት የሆናትን ሕልም አየች። ይህ አጋጣሚ አሁንም በጀምበር ትውስታ ውስጥ አለ፦ "የግብረ ገብ ትምህርት ጥሩ አድርገው የሚያስተምሩን አንድ የተማሩ መነኩሴ ነበሩ። ያኔ በመንግሥት ትምህርት ቤት መንፈሳዊ ትምህርት ይሰጥ ነበር። ወቅቱ የሁዳዴ ጾም መግባደጃ የሕማማት ሰሞን ነበር። በጸሎተ ኀሙስ ቀን ትምህርት ሊዘጋ ገደማ መምህሩ ተውኔታዊ በሆነ መንገድ ስለ ስቅለቱ ሲያስተምሩ፣ ጌታችን የተቀበለው ስቃይ በሙሉ ተሰማኝ። መምህሩም ደጋግመው፣ <ይህን ላደረገልን አምላክ ምንድን ነው የምናደርግለት?> ይሉን ነበር። <እውነት ግን ምንድን ነው የምናደርግለት?> የሚለውን ጥያቄ እያሰላሰልሁ ወደ ቤቴ ተመለስሁ። ...ሌሊት ግልጽ ብሎ የሚታይ ሕልም አየሁ። <በአንዱ በእኔ አቅም ለድኻ አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ" የሚል ቃልም፣ መዝሙርም ተሰማኝ።"



ያቺ የአቡሊ መሪና ረዳት የነበረችው ባለ ራእይ ልጅ ዛሬ፣ አንቱ የተባለች ትልቅ ሰው ሆናለች። አንቱታው ከዕድሜ መብሰል ጋር ብቻ የመጣ አይደለም። በታላቅ ትምህርት ታግዞ፣ የድኾች ረዳትና ጠበቃ በመሆን የተገኘ ስም እንጂ፤ ይህች የቀድሞ የአቡሊ መሪ በአሁኑ ሰዓት «በሙሉ በተቀነባበረ ዘዴ የከተማ ልማት ፕሮጀክት» መሥራች፣አስተባባሪና ርዳታ አሰባሳቢ የሆኑት ዶክተር ጀምበር ተፈራ ናቸው።

ሚያዚያ 23 ቀን 1935 ዓ.ም እናታቸውና አባታቸው ለስደት ሄደው በነበሩበት በማዳጋስካር ደሴት ተወለዱ። ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍልን በአዲስ አበባ እቴጌ መነን ትምህርት ቤት፣ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል ትምህርትን ደግሞ ሐረር የሺ እመቤት ትምህርት ቤት የተከታተሉ ሲሆን የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንግሊዝ አገር በሰሜን ዌልስ ውስጥ ከሚገኘው ‹ክላራንደን› በሚባል የክርስቲያን ትምህርት ቤት ተምረው አጠናቀቁ።

ዶክተር ጀምበር ከዚህ በኋላ የተማሯቸው ትምህርቶች አሁን እየሠሯቸው ካሉት ሥራዎች ጋር ዝምድና ያላቸው ናቸው። ይህንንም እውነት እንዲህ በማለት ይገልጹታል። "...ትምህርቴ ከነበረኝና ካለኝ የሥራ ሂደት ጋር የተሳሰረ ነው ማለት እችላለሁ። መጀመሪያ የገባሁት ወደ ነርስነት ሙያ ነው። ነርሲንግ የተማርሁትም እንግሊዝ አገር ሁለት ቦታ ነው። እግዚአብሔር ወደ እዚህ ሙያ ለምን እንዳስገባኝ ወደ ኋላ ሳየው ካለኝ ሕልም [ርእይ] አንፃር ለብዙ ጥቅም እንደ ሆነ ተገንዝቤያለሁ።"

ዶ/ር ጀንበር እንግሊዝ አገር ነርስነትን ትምህርት ከተማሩ በኋላ በቀጥታ የተመለሱት ወደ አገራቸው ነው። ይህንንም አጋጣሚ እስታውሰው ሲናገሩ፣ "በዚያን ወቅት ወደ ውጪ አገር ወጥቶ በዚያ ለመቅረት የሚያስብ ብዙም ሰው አልነበረም። የኔም የሁልጊዜ ሕልም ወደ አገሬ ተመልሼ ከድኾች ጋር መሥራት ነበርና ከዘጠኝ ዓመት ቆይታ በኋላ ወደ አገሬ ተመለስሁ" ብለዋል።





ወደ አገራቸው ተመልሰው ሥራ ላይ እንዴት እንደ ተሰማሩ እንዲህ በማለት ያወሳሉ፤ "በጊዜው ሁሉም ሰው ይመርጥልኝ የነበረው የውጪ ድርጅቶችን ወይም ደግሞ ትልልቅ ካምፓኒዎችንና የመሳሰሉ ቦታዎችን ነበር። ትዝ ይለኛል፤ ሥራ እየፈለግሁ ባለሁበት ወቅት እንቴ የምትሠራው በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ ነበር። ‹የት ለመሥራት ትፈልጊያለሽ?› አለችኝ። ከአንድ ሐኪም ጋር ተገናኝተን፣ ‹ጳውሎስ ሆስፒታል የድኾች ሐኪም ቤት ነው። ጃንሆይ ለድኾች መታከሚያ እንዲሆን ብለው ያሠሩት ነው› እዚያ ነው መሥራት የምፈልገው› አልኳት። የጳውሎስ ሆስፒታል የሚተዳደረው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጊ ድርጅት ሥር ነበር ። እንደ አጋጣሚ ከበጎ አድራጊ ድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ጋር እንግሊዝ አገር እንተዋወቅ ነበር። እርሱ ‹ኢጁኬሽናል አታሼ› ነበር። ‹እስኪ ይህን ሆስፒታል ልግባና ልየው!› ብዬ ስሄድ፣ ‹አሁን በቃ አንቺ እዚያ ገብተሽ ለእነሱ መብት እቆማለሁ እያልሽ ትረብሺናለሽ። እባክሽን እዚያ አትግቢ። ሌሎች ሐኪም ቤቶች አሉና አማርጠሽ ግቢ› አለኝ። ‹አይ! እኔ የምፈልገው ተልእኮዬ ከድኾች ጋር መሥራት ስለ ሆነ የምገባው እዚያው ነው።› አልሁት። ‹ልብሽ ከፈቀደ እንግዲህ ምን ይደረጋል› በማለት እየቀለደ ለሆስፒታሉ አስተዳደርና ሥራ አስኪያጅ ነገራቸው። እነርሱም ከውጪ አገር ተመልሼ ስለ መጣሁ የተሻለ በሚሉት፣ ‹የሰርጂካል የሴቶች ወርድ› በሚባል የሥራ ክፍል ውስጥ ኀላፊ ሆንሁ።›" ዶ/ር ጀምበር ያኔ ጳውሎስ ሆስፒታል ገብቶ መሥራት የፈለጉት በሙያቸው ድኾችን ለመርዳት ከነበራቸው ብርቱ ፍላጎት የተነሣ ቢሆንም ከገቡ በኋላ ግን ያሰቡትን ከግብ ለማድረስ ብርቱ ዕንቅፋት ገጥሟቸዋል።

ዶ/ር ጀምበር እንግሊዝ አገር በቆዩባቸው የትምህርትና የሥራ ዓመታት ውስጥ ያዳበሩት አንድ ልምድ ነበራቸው። "በናሽናል ሄልዝ ሰርቪስ› ውስጥ ሠርቼ ነበር" የሚሉት ዶ/ር ጀምበር፣ በዚያ ተቋም ውስጥ አንድ ቡቱቶ የለበሰ ሰው፣ ከዩንቨርሲቲ ፕሮፌሰር፣ ከገበሬ፣ ከሐኪምና፣ ከጄኔራል አጠገብ ተኝቶ እኩል እንክብካቤ ሲደረግለት



አይተዋል። እዚህ ሲመጡ የገጠማቸው ግን የተገላቢጦሽ ነበር።

"በእኔ መረዳት ሐኪም ቤት ማለት ማንኛውም በሽተኛ እንክብካቤ ተደርጎለት የሚታከምበት ስፍራ እንጂ በመደብ የሚለያይበት፣ ድኻው እንደሚሆን ይሆናል የሚባልበት ቦታ አይደለም። ጳውሎስ ሆስፒታል ውስጥ ያሉት ታካሚዎች ከክፍለ አገር ድኻ ስለ መሆናቸው ተመስክሮላቸው የሚመጡ ናቸው። እንደ ገባሁ በማየው ነገር ሁሉ በጣም ማዘን ጀመርሁ። ምክንያቱም ሠራኛው ለድኾች የሚሰጠው እንክብካቤ በጣም አነስተኛ ነበር።" "በዚህም በጣም መበሳጨት ጀመርሁ" የሚሉት ዶ/ር ጀምበር ከሠራተኞች ጋር ጭራሽ መግባባት እንዳልቻሉ የሚያሳየውን ሐሳባቸውን እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

"ትዕግሥቱ ብዙም የለኝም። ወደ ኋላ ሄጄ ሳስበው አንደኛ ልጅነት አለ፤ ሁለተኛ ተልእኮ አለኝ ብዬ ነው የገባሁት። ወደ ሆስፒታሉ የሚገባው ዕቃ ለድኾቹ አይሆንም። በየአልጋው ላይ የበሰበሰ ፍራሽ ይታያል፣ የሕክምና አሰጣጡ ጥንቃቄ በጣም የሚያሳዝን በመሆኑ፣ ከሠራተኞቹ ጋር ሁልጊዜ እጋጭ ነበር። የዩጎዝላቪያ የሕክምና ባለሙያዎች ነበሩ። በሽተኛ አያያዛቸው በጣም ያሳዝናል። ድኻውን እንደ ፈለጋቸው ቢያደርጉት አይከሰሱም። የሙያ ሥነ ምግባር አልነበራቸውም። ከእነርሱ ጋርም መጋጨት ጀመርሁ። ይሄ ሁሉ ሰልችት አለኝ። ሠራተኛው ሥራውን ለቆ በወጣ ቍጥር ‹በአንቺ ምክንያት ነው የለቀቀው› በማለት ይቀልዱብኝ ጀመር።"

ዶ/ር ጀምበር ስድስት ወር በእንደዚህ ዐይነት ሁኔታ ከሠሩ በኋላ ለሌላ ኀላፊነት ታጩ። ሆኖም ይህን ኀላፊነት በቀላሉ የሚቀበሉት አልሆነም። ይህንንም እንደሚከተለው ይገልጹታል "በዚህ መልኩ ስድስት ወራትን ካስቈጠርሁ በኋላ አስተዳደሩ ጠራኝ። ‹አንቺ ምንም ነገር ስላልጣመሽ፣ እስኪ ኀላፊ ሁኚና ይሄን አስተዳድሪ› አለኝ። እኔም መለስሁና ‹የበጠበጥኋችሁ ኀላፊነት ፍለጋ አይደለም። በጠቅላላው እንኳን ኀላፊ ሆኜ ይቅርና ያለሁበትን ክፍል ለመለወጥ





ተቸግሬያለሁ። ምክንያቱም አዳሪ ሆኜ ስሠራ፣ ሁሉንም ክፍሎች አይቻቸዋለሁ። ከሁሉም ጋር እንደ ተጣላሁ ነው። በሠራተኞቹ አስተሳሰብ ድኻ ሌሊት አይታመምም። በአንድ ሌሊት አራትና አምስት ሰው ሞቶ ይገኛል። በሽተኛው ሲጠራቸው አይመጡለትም። እንደውም 'ቀን ተረድተሃል አታስቸግር' ይባል ነበር። እኔም ተነስቼ የድኻ ህማም ሌሊትና ቀን ለይቶ ነው ወይ የሚመጣው ብዬ በቁጣም በማሾፍም እናገር ነበር። በጣም ብዙ ጭቅጭቅ አለ። እና ግዴለህም እኔ ብቀርብህ ይሻላል› አልኩት።"

አስተዳዳሪው በጊዜው ሲስተር ጀምበር ከሠራተኞች ጋር አለመግባባትን የሚፈጥሩት የአሠራር ለውጥ ለማምጣትና ድኻው ኅብረተ ሰብ በአግባቡ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ለማድረግ እንደ ሆነ ያውቅ ነበርና፣ "ጠቅልዬ የኀላፊነቱን ቦታ ካልሰጠሁሽ፤ ሁሉም ነገር አልጥምሽ ስላለ እስቲ ግቢበትና እንይሽ ሚዳውም ይኸው ፈረሱም ይኸው" ብሎ ግትር አለ። ይህን የተረዱት ዶ/ር ጀምበር ወደ ሥልጣኑ ለመምጣት ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀመጡ።

"በመጀመሪያ ሐኪም ቤቱን በሙሉ ላጥናና ያሉትን ችግሮች በሙሉ ጽፌ የሚሟሉትን ካላሟላችሁ በጭራሽ ኀላፊነቱን አልወስድም አልሁት። ‹ለምን?› አለኝ። ‹ነዋ! ቅያሪ አንሶላ በሌለበት፣ ለቁስል እንኳ መለወጫ በቂ ቍሳቍስ በሌለበት፣ ቤቱ ተሰንጥቆ ሲወድቅ አንድ ኀሙስ በቀረውና ብዙ ችግር ባለበት ሁኔታ ምን ተብሎ ነው የሚገባው?› ‹ቢቃ እሺ እንዳልሽ ይሁን!› አለኝ። ያሉትን ችግሮች በሙሉ ጻፍሁና የሚያስፈልገው ወጪ ወደ 32 ሺ ብር ታሰበ። ‹ወደ 24 ሺ ብር አለን፤ ሌላውን አላውቅም!› አለኝ። ቀሪውን ብር ከማውቃቸው ሀበሾችና ፈረንጆች በግሌ ሳሰባስብ ወደ 10 ሺ ብር አገኘሁ። በብሩ በጠቅላላ ሐኪም ቤቱን በሙሉ አደስን። ያልተሟሉ ዕቃዎችንም አሟላን። መቀጠር የሚገባቸውን ባለሙያዎች ቀጠርን፣ ሥልጠና ለሚያስፈልጋቸው ሠራተኞችም ሥልጠና ሰጠን። ‹ሩቱን› አወጣን፤ ሁሉም ነገር ተስተካከለ።"



"የሚገርመው ነገር፣ አሁንም የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር አልቀነሰም።" የሚሉት ዶ/ር ጀምበር በራሳቸው እነሣሽነት ሆስፒታሉን በብዙ ይለውጡት እንጂ ሠራተኞቹን ሊለወጡ ባለመቻላቸው በውትር ያዝኑ እንደ ነበር ይናገራሉ፤ "የሊሊቱን ችግር ለይተን አወጣን። <በሽተኞች ቀንም፣ ሌሊትም መረዳት አለባቸው!> አልን። ሰዎቹ ግን አልተለወጡም ነበር። በተለይ ከዲሬክተሩ ጋር ጦርነት ሆነ፤ ዩጎዝላቪያዊ ነው። በድኻ ላይ የተለየ ንቀትና ጥላቻ አለው። <ለእነርሱ ይሄ ሁሉ እንክብካቤ ምንድን ነው?> ይለኛል። በቃ ጦርነት ነው!"

በጊዜው ይህን የሚፈጽሙት በዕድሜ ካለመብሰልና ከትዕግሥት ማጣት የተነሣ እንደ ነበረ ቢናገሩም ለዚህ ሁሉ ግን ያነሣሣቸው የነበረው ሁኔታዎች ፍትሓዊ አይደሉም ብለው ከማመናቸው የተነሣ እንደ ነበረ ይገልጻሉ። ዶ/ር ጀምበር አንድ ቀን የገጠማቸውን አጋጣሚ እንዲህ ይገልጹታል፤ "በአንዱ ሌሊት የተለየ ልብስ ለብሼ ድንገታዊ ቁጥጥር አደርጋለሁ ብዬ ወደ ሆስፒታል ሄድሁ። ሆስፒታሉ በር ላይ ደርሼ የመኪናዬን ጡሩንባ ስነፋ፣ ዘበኛው ለእኔ በሩን መክፈቱን ትቶ ወደ ውስጥ ገባና አስታማሚዎችን በሙሉ ከእንቅልፋቸው ቀሰቀሳቸውና ተመልሶ መጥቶ ከፈተልኝ። ስገባ በጣም አዘንሁ። ቍስለኛው የቍስሉ ፋሻ አልተለወጠለትም፤ አንሶላው አልተለወጠለትም። አልጋው በስብሶ ይሸታል። በጣም ሆድ ባሰኝ። ባለቤቴ በሁሉም ሥራዬ ከጐኔ ነበርና ሁሉን ነገር በዝርዝር አጫወትሁት። "እኔ ከእግዚአብሔር ጋር የምጣላበት ነገር ሊሆን ነው። እነዚህን ሰዎች ቀና በማስብና ሥልጠና በመስጠት ብቻ መለወጥ አልቻልሁም። ባለቤቴም፣ <አይ የቻልሽውን ያህል ሞክርሽ እንግዲህ ምን ታደርጊዋለሽ! አለኝ። ከሥራው ጫና በተጨማሪ በወቅቱ ነፍስ ጡር ስለ ነበርሁ እርግዝናዬ በሥራ ድካም ሳቢያ ትንሽ ውስብስብ ነገር ገጠመው።"



ጳውሎስ ሆስፒታልን ለመለወጥ ብዙ የታገሉት ዶ/ር ጀምበር ከዚህ በኋላ ብዙም አልቈዩም ከሦስት ዓመት ትግል በኋላ ። "ቀይ



መስቀል የጤናና የሶሻል ክፍል ኀላፊ ይፈልጋል ሲባል፣ እዚያ ደግሞ ገባሁ" ይላሉ። ይሁን እንጂ እዚያም ቢሆን የጠበቁት ነገር እንዳልገጠማቸው ያስታውሳሉ፤ "እዚያም ያጋጠሙኝ ችግሮች ነበሩ። የአንቡላስ ሰርቪስ ለድኾች አለ፤ ሆኖም ግን ተገቢው አገልግሎት አይሰጥባቸውም። የድርጅቱ የማሠልጠኛ እንቅስቃሴም በጣም የተሸበበ ነው። በጠቅላላ ስለ ድኽነት ያላቸው ግንዛቤ የተዛባ ነበር። ለምሳሌ አንድ የአንቡላንስ ሹፌር አንድ ድኻ ታሞ ደውሎለት ጊዜውን አባክኖ ሄዶ ለድኻው በሰዓቱ ሳይደርስለት ቀርቶ እንደ ሞተ አውቃለሁ። ስውየውንም ለመክሰስ ጥረት ሳደርግ ሠራተኛው በሙሉ ተንጫጫብኝ። ከዚያ በኋላ የአንቡላስ ቍጥር አስጨመርሁ። ተጨማሪ የአንቡላንስ ሾፌሮችንም አሠለጠንሁ ሬድዮ ኮሙኒኬሽንም አስገባሁ።"

ዶ/ር ጀምበር ከዚህ በኋላ መምራት የጀመሩት ሕይወት መራራ ነበር። ወቅቱ አብዮቱ የተከሠተበት ስለ ነበር ባለቤታቸው ለእስር ተዳረጉ። ይህም በሥራቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማሳደሩን እንዲህ በማለት ይገልጹታል፤ "አብዮቱ ተከሠተ፤ ባለቤቴም ታሰረ። ያኔ በእነርሱ አባባል <የጨቋኙ ወገን> ስለ ሆንሁ የአንቡላንስ ሾፌር ሲያጠፋ እንኳ መናገር አልችልም ነበር። የማይከፈልበት ቦታ ሕዝቡን ያስከፍላሉና ሌብነትም ዕቃም ሲሰረቅ አብረው ይተባበሩ ነበር። ብዙ ችግሮች ስለ ነበሩ ሥርዓት ለማስከበር በጣም ችግር ገጠመኝ። ሌሎች ሥራዎችም ነበሩ፤ ለምሳሌ፣ ለሰብአዊ መብት መከበር ቀይ መስቀል ከሚያከናውናቸው ተግባሮች አንዱ ወታደሮችን ማስተማር ነበር። እነርሱን እንዳላስተምር ከለከሉኝ። በሁሉም ነገር አልተመቸኝም።"

በዶ/ር ጀምበር ላይ የደረሰው ጫና በዚህ አላበቃም። የባለቤታቸው ለእስር መዳረግ ሳያንስ እሳቸውም ወደ ወህኒ ቤት ወረዱ። ይህ አጋጣሚ ለእርሳቸው ብቻ ሳይሆን ለዘመዶቻቸውም ልብ የሚሰብር ነበር። ሁኔታውን እንዲህ ገልጸውታል "መጨረሻ ላይ እኔም ራሴ አራት ልጆቼን ትቼ ከርቸሌ እስር ቤት ገባሁ። የመጨረሻ ልጄ አንድ ዓመት ከሦስት ወሯ ነበር። ከእርሷ በላይ ካለችው ልጄ ጋር



የነበራቸው ልዩነት የአንድ ዓመት ብቻ ነበር። ትልልቆቹ ደግሞ የሰባትና የስምንት ዓመት ልጆች ነበሩ። እና ትቻቸው የገባሁት መጥፎ ሁኔታ ላይ ነው። የታሰርኩ ዕለት ትዝ ይለኛል፤ ፈጣሪዬን ክፉኛ አማረርሁ። ከእግዚአብሔር ጋር ትልቅ ጦርነት ውስጥ ገባሁ።" ዶ/ር ጀንበር በወቅቱ የታሰሩበትን ምክንያት ሲጠየቁ እንኳን እርሳቸው አሳሪዎቹ ራሳቸው በውል እንደማያውቁት ይናገራሉ፤"ከውጭ አገር ሰዎች ጋር ባለኝ ግንኙነት፣ ቀይ መስቀል በመሥራቴ፣ ባለቤቴ በመታሠሩ ነው መሰል ከእኔ ብዙ ዐመፅ ይጠብቁ ነበር። እሥር ቤት ስገባ የክስ መዝገቤ ላይ ምክንያቱ አልተገለጸም ነበር። ከእሥር ስፈታም የተሰጠኝ ደብዳቤ ‹የአብዮቱን ሂደት ታደናቅፋለች› የሚል ነበር። ቀይ መስቀል በመሥራቱ ባለቤቱ በታሰረበት ወቅት መጽሔትና የመሳሰለው ነገር ወደ እሥር ቤት እንዳይገባ ተከልክሎ ነበር። እንደ ጥፋት ተቈጥሮ ለእሥር የዳረገኝ ቢያንስ ቢያንስ እንዲህ ዐይነት ነገሮች እንዲሚሉ ዓለማቀፍ የቀይ መስቀል ማኅበርን፣ "የእነዚህ እስረኞች መብት ይከበር!" ብዬ ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል ትክክለኛ ፍትሕ እንዲኖር መጠየቁ ይሆናል። በኋላ እንደ ሰማሁት ሪፖርት ያደረገችው አምነስቲ ኢንተርናሽናልን የጠየቅሁበትን ደብዳቤ ያጻፍኋት ሴትዮ ናት።"

ዶ/ር ጀምበር በእስር ላይ በነበሩበት የመጀመሪያ ሰሞን ከባድ ሐዘን ያመጣባቸው ነገር ቤተ ሰባቸው በተለይ ሕፃናት ልጆቻቸው በዚህ መልክ መለያየታቸው ነበር። ያለ እረኛ፣ ያለ አባትና እናት በውል ነፍስ የማያውቁ ሕፃናት እንዴት ይሆኑ ይሆን? በእጅጉ ያስጨነቃቸው ይህ ነበር። "እስር ቤት ከገባሁ በኋላ እንዴት ዝም ብዬ እቀመጣለሁ? ባልም ሚስትም ታስረው እንዴት ተብሎ ነው ልጆች ብቻቸውን የሚኖሩት? የቤተ ሰብ ዋጋ ምንድንነው? ብዬ ለማሰብ ሞከርሁ፤ መጨረሻ ላይ ለአንድ ወታደር አቤት ስል፣ ከት ብለው ሣቁብኝ። ‹ሁሉንም ነገር ያውቃሉ። አውቀው ነው ያሰሩሽ። እንኳን መታሰር ይቅርና ገና መረሸንም ይደርስብሻል።› ብለው ቍርጡን ሲነግሩኝ ለመጀመሪያ ጊዜ በጣም ስቅስቅ ብዬ አለቀስሁ። ልጆቼን አሰብሁ፤ እናቴ አረጋዊት





ነበረችና አሳዘነችኝ፤ ታላቅ ወንድሜ እኛን ለመርዳት ብሎ ከካናዳ ድረስ ትምህርቱን አቋርጦ መምጣቶ ሳየው አሳዘነኝ። አልቅሼ ስጨርስ፣ እንደ ጸሎት ጸለይሁ፦ ‹ለምን እንደ ሆነ ያመጣኸኝ አላውቅም። በፈለግኸው ነገር ተጠቀምብኝ!› አልሁ።"

ከዚህ በኋላ ዶ/ር ጀምበር ነገራቸውን ሁሉ ለፈጣሪያቸው ሰጥተው ፊታቸውን በሕፃንነታቸው ወቅት ወዳዩት ራእይ መለሱ። በተማሩት ሙያ ተጠቅመው ከሌሎች ባልንጀሮቻቸው ጋር በመሆን የጤና ባለሙያዎች አሠለጠኑ፤ ከእስር ቤት ውጪም ከወዳጆቻቸው ጋር በመጻጻፍ ለወህኒ ቤቱ ታራሚዎች የሚያገለግል ክሊኒክ አቋቋሙ። በአጠቃላይ በእስር ቤቱ ውስጥ በጤናና በግል ንጽሕና አጠባበቅ ዘርፍ የነበራቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነበር። ይህንንም እንደሚከተለው ይገልጹታል።

"የጤናው ሁኔታ እጅግ በጣም አሳሳቢ ነበር። ለእስረኞች የሚሰጠው እንክብካቤ የሚያሳዝን ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ወህኒ ቤቶች በከፋ ሁኔታ ላይ ነበሩ። በመሆኑም ተቃውሞዬን አሰማሁ። ‹ፈቃድ ስጡንና የጤና ባለሙያዎች እናሠልጥን!› አልሁ። በዚያ ወቅት በአጋጣሚ በመካከላችን በተለያዩ የሕክምና ዘርፎች የሠለጠኑ ባለሙያዎች ስለ ነበሩ ዕውቅና እንዲሰጡን አደረግሁ። የማውቃት አንዲት ወዳጅ ነበረችኝ። ገንዘብ ሰጠችኝና ክሊኒክ ተሠራ። ሥልጠናውንም ሰጠን። የመጀመሪያ ሕክምና ርዳታ መስጠትም ጀመርን። ተጻጽፌ እየለመንሁ አንድ ቤተ መጻሕፍትም አሠራን። ዕድገት በኅብረት ዘምተው የመጡ ብዙ ሴት እስረኞች ነበሩ። ከእነዚህ ውስጥ አርግዘው የተመለሱ ብዙ ነበሩ። በወሕኒ ቤት ልጆችንም ስናዋልድ ከ23ቱ 13ቱን ያዋለድኋቸው እኔ ነበርሁ። የምናዋልደው እየለመንን፣ እስረኛው ጨርቁን ቀዶ እየሰጠንም ነበር ።"

የዶ/ር ጀምበር የወህኒ ቤት አገልግሎት በጥቂቱ ይህን ይመስል ነበር። እርሳቸውም ዛሬ ላይ ሆነው ስለ ወህኒ ቤት ቈይታቸው ሲያስቡ



በብዙ ነገር ይደመማሉ። የሠሯቸውን ነገሮች ወደ ኋላ መለስ ብለው ሲያስቡም "ምናልባት ለዚህ ይሆናል ፈጣሪዬ የፈለገኝ!" ይላሉ። "ልጆቼን ዘመዶቼና ወዳጆቼ፣ እንግሊዝ አገርም ያሉ ሰዎች እያዋጡ ይረዱቸው ነበር። በተለይ ትልቋ እኅቴ ከመሞቷ በፊት ከጐናቸው ነበረች። ልጆቼ እየተረዳዱ ሲቈዩ፣ እኔ ደግሞ እስር ቤት ይሄን ስሠራ ቈየሁ።" የሚሉት ዶ/ር ጀምበር ከእሥር በተፈቱበት ዕለት መፈታታቸውን ለማመን ተቸግረው እንደነበር እንዲህ ይገልጹታል፦

"ከእስር ቤት በተፈታሁ ዕለት መፈታቴን በቍራሽ አላመንሁም። ተስፋ ቈርጬ ነበር። አንዲት የመኢሶን አባል ተደብድባ ከባድ ጒዳት ደርሶባት ስትመጣ ብቻዬን ሕክምና የሰጠኋት እኔ ነበርሁ ። ብዙ ከወተወትሁ በኋላ አንቡላንስ መጥቶ ይወስዳታል ተብሎ ተነግሮኝ ስለ ነበር ደጋግሜ ወደ በር በማይበት ጊዜ የበር ጠባቂዋ ትጠራኝና <ተፈተሻል!> ትለኛለች። "ቀልደኛ ነሽ!" አልኋት። <ኧረ እባክሽ ተፈተሻል እኮ ነው የምልሽ!" ትለኛለች። <ሴትየዋ ምንድነው የምትቀልደው!?> አልሁ። "እነ እከሌ፣ እነ እከሌ ተፈትተው ልብሳቸውን እየለበሱ ነው። አንቺም ተፈተሻል" አለችኝ። በወቅቱ ለበሽተኛዋ አንቡላንስ ይመጣላታል ተብዬ እየጠበቅሁ ነበር። ተፈትቼ ልወጣ ስል <ይቺ ሴትዮ አሁንም እኮ አንቡላንስ አልመጣላትም> ስል፣ <ኧረ እባክሽ ሂጂ! የተፈታ እስረኛ እዚህ አይቀመጥም> አሉኝ። <እሺ አንድ ነገር አድርጉላት> ብዬ ወጣሁ።" ዶ/ር ጀምበር ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድና እንግልት በኋላ ቢፈቱም፣ ከእስር ቤት ቈይታቸው ብዙ ትምህርት እንደ ቀሰሙ ይናገራሉ፦

"እሥር ቤት ከመግባቴ በፊት ቀና የሆኑ ነገሮች በውድም ሆነ በግድ መፈጸም አለባቸው ብዬ የማምን ሰው ነበርሁ። አንድ ሰው ከታዘዘ መሥራት አለበት። ካልሠራና ጥሩ ነገርን ካጐደለ መቀጣት አለበት ነበር የምለው። እስር ቤት ከገባሁ በኋላ ግን ነገሮችን በተለየ አቅጣጫ የምመለከትበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ምንም እንኳ እንዲሠራ የምፈልገው ነገር ቀና ቢሆንም፣ ቡድኑ በመሠረታዊ እምነቱ ላይ የጋራ መንፈስ





ከሌለው ሥራ ሊሠራ እንደማይቻል ተረዳሁ። የሚሻለው "እኔ ሀውቅልሃለሁ፤ እኔ አዝንልሃለሁ" ሳይሆን እርሱ፣ እርሷና እነርሱ ምን ይፈልጋሉ? በማለት በልብ ትርታቸው ላይ ተመሥርቶ መሥራት ነው ወደ ሚለው ድምዳሜ ላይ ደረስሁ። ከእስር ቤት የወጣሁት የቡድን ሥራ ትልቅ ውጤት እንደሚያስገኝ ተረድቼ ነው። ዛሬ የምንሠራቸውም ሥራዎች የቡድን ሥራ ውጤቶች ናቸው።"

"በሙሉ በተቀናባበረ ዘዴ የከተማ ልማት ፕሮጀክት" የተቋቋመው እነዚህን ሁሉ መሰናክሎች ባለፉት በዶ/ር ጀምበር ነው። በንግግራቸው መካከል "እኛ" እንጂ "እኔ" ሲሉ የማይደመጡት ዶ/ር ጀምበር ለዚህ ፕሮጀክት ስኬታማነት ምንም እንኳ የእርሳቸው ራእይ መነሻ ቢሆንም በዙሪያቸው ያሉ ሰዎች ሚና ግን ቀላል እንዳልሆነ አዘውትረው ይናገራሉ፤ ይህንንም በጥሩ ቋንቋ ሲገልጹት፣ *"ራእይን ከሚጋራ ሰው ጋር ራእይን ለጠኝ!"* ይሉታል።

ወ/ሮ ዘነበ ወርቅ ብሥራት ይባላሉ፤ በሙሉ በተቀናባበረ ዘዴ የከተማ ልማት ፕሮጀክት ሥር በተቋቋመው፣ "ኢኒስቲቲዩት ፎር ኧርባን ምርከርስ" /በከተማ ልማት ሠራተኞች ኢኒስቲቲዩት/ አካዳሚክ ዲን ናቸው። ከዶ/ር ጀምበር ጋር የሚተዋወቁት ከልጅነታቸው ጀምሮ ነው። "ዶ/ር ጀምበርን የማውቃቸው በልጅነታችን ከግርማዊት እቴጌ መነን ትምህርት ቤት ጀምሮ ነው። ከወጣትነት ዘመናቸው ስንሣ፣ ጀንበር አስተዋይ፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩ፣ ብዙ የሚያነቡ፣ በትምህርታቸውም ጠንካራ ሴት ናቸው። ዶ/C ጀምበር ድኾችን መርዳት ከልጅነታቸው ጀምሮ አብሮ የመጣ ባሕርያቸው ነው። ጀምበር በትምህርት ቤት አካባቢ ቤተ ሰብ የሌላቸውን ተማሪዎች ለበዓል ጊዜ እቤታቸው ይዘው በመሄድ በዓሉን ከራሳቸው ጋር አብረው እንዲያሳልፉ ያደርጉ ነበር። ልጅ እያለን የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሰንበት ትምህርት ቤት አባል ነበርን። እዚያ ውስጥ ደግሞ ለድኾች ይሆናል ተብሎ እጅ ሥራ እየተሠራና እየተሸጠ ለርዳታ ገንዘብ የሚዋጣበት ሁኔታ ነበር። በወቅቱ በዶ/C



ጀምበር በኩል የሚደረገው እስተዋፅኦ የማይታመን ነበር።"

ወ/ሮ ሐረገ ወይን ትባላለች። ረዳት የሕዝብ ግንኙነት ኀላፊ ናት። በፕሮጀክቱ ውስጥ መሥራት ከጀመረች አምስት ዓመታትን አሳልፋለች። ስለ ዶ/ር ጀምበር ተፈራ ስትናገር በከፍተኛ አድናቆት ነው፤ "በጣም ትዕግሥተኛ ናቸው፤ አይደክሙም፤ አይሰለቻቸውም፤ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ተስፋ ያደርጋሉ። አንድ ነገር አልተሳካልኝም ብለው ተስፋ መቍረጥ ብሎ ነገር በምንም መልኩ አያውቁም። እኔ እርሳቸውን ብሆን ኖሮ ሁሉንም ነገር ጥርቅምቅም አድርጌ የምጠፋ ይመስለኛል። በብዙ መንገድ ነገሮች ሲወሳሰቡባቸው በትዕግሥት፣ ‹እግዚአብሔር ያውቃል፤ እርሱ ይፈጽምልናል፤ ብዙ ፈተና አሳልፈናል፤ ወደ ፊት ቀጥሉ!› የሚሉ ጠንካራ ሴት ናቸው።"

በሙሉ በተቀናባበረ ዘዴ የከተማ ልማት ፕሮጀክት ተግባርን ስንመለከት፣ ማዕከሉ በጣም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወገኖችን ከመርዳት አኳያ የሚያከናውናቸው ተግባራት እያሉ ናቸው። በቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ በማር ቤት አካባቢ በቀበሌ 08 እና በልደታ ክፍለ ከተማ፣ በተክለ ሃይማኖት አካባቢ በቀበሌ 30፣41፣42 እና 43 ሥር ባሉ ቀበሌዎች ውስጥ ካሉት የአረጋውያን ማቈያ ማእከላት በተጨማሪ በማኅበረ ሰብ እድገት፣ በመሠረተ ጤና እንክብካቤና በአካባቢ ልማት ዘርፎች በስፋት የሚንቀሳቀስ ፕሮጀክት ነው።

ፕሮጀክቱ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ የልማት ሥራዎችን አከናውኗል። ካከናወናቸው ተግባራት መካከልም፣ የአረጋውያን መዋያ ማእከላት፣ የወጣቶች ሙያ ማሠልጠኛ ማእከል፣ ቤተ ንባብ፣ አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የሕፃናት መዋያ፣ የጤና ኬላ፣ የውሃ ቦኖ፣ የአካል ጉዳተኞች ማሠልጠኛ ማእከል፣ እጅግ የተጎዱና ለሰው ልጅ መኖሪያ የማይሆኑ ቤቶችን በአዲስ መልክ መሥራትና መጠገን፣ የጋራ መጠቀሚያ የሆኑ ማዕድ





ቤቶችና መጸዳጃ ቤቶችን መሥራት ይጠቀሳሉ።

ዶ/ር ጀምበር ከነርስነት ሙያ ባሻገር የድኅረ ምረቃ ትምህርታቸውን በእንግሊዝ አገር ማንችስተር ዩኒቨርሲቲ ተከታትለው በማጠናቀቅ ኤም ፊል/ማስተርስ ዲግሪ አግኝተዋል። አሜሪካን አገር ፊላዴልፊያ ‹ዶክተር ኦፍ ሚኒስትሪ› ያገኙ ሲሆን ፤ ይህም እስካሁን ካጠኗቸው የትምህርት ዘርፎች ለየት ያለ ሐሳብ ነው። የዶክትሬት ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፋቸውም (ቴሲስ) *"Entering The world of poverty"* በሚል ከድኻም ድኻ የሆኑ ሰዎች እንዴት በእኛ ፍልስፍና ሊረዱ ይችላሉ? በሚል የማኅበራዊና የአካባቢ ልማት ዘርፎችን የሚዳስስ የሁለአናዊ አገልግሎት ጥናት ነው። በጥናቱ ላይ ሌሎች የሃይማኖት ተቋማትም እንዴት በድኽነት ላይ ተነስተው መረባረብ እንዳለባቸው አመላክተዋል።

ዶ/ር ጀንበር እንደ ሕይወት ምሳሌ ወይም "ሞዴሊ ናቸው" ብለው የሚያነሡአቸው በርካታ ሰዎችን ነው። ከነዚህ ሰዎች መካከል በቀዳሚነት እናታቸውን ይጠቅሳሉ፤ "በሕይወቴ ላይ ምሳሌ ብዬ የማነሳቸው አንደኛ እናቴን ነው። የተወለድሁት ከደሀና ቤተ ሰብ ነው። ያደግሁት ተቸግሬ አይደለም። ከሕፃንነቴ ጀምሮ ድኽነት ፍትሓዊ እንዳልሆነ እንዲገባኝ ያደረገችው፣ በአንጻሩ ደግሞ የኔን የምቾት ኑሮ እንዲገባኝና እንዳመሰግን፣ ሌሎች ደግሞ ምን ያህል እንደሚቸገሩ እንድገነዘብና ከጎረቤቶቼ ጀምሮ ያለኝን እንዳካፍል፣ የነሱን ችግር አይቼ እንድረዳ በብዙ መንገድ የረዳችኝ እናቴ ናት።"

በሁለተኛነት እንደ ምሳሌ የሚያዩአቸው የከንቲባ ገብሩ ልጅ ወ/ሮ ሰንዱ ገብሩን ነው። ከእርሳቸው የተማሩት ጥንካሬንና ጽናትን እንደ ሆነ ዶ/ር ጀምበር ሲናገሩ፤ "እርሳቸው የእቴጌ መነን ትምህርት ቤት የመጀመሪያዋ ሴት ርእሰ መምህር ናቸው። እርሳቸው በዚያን ወቅት ምናልባት እናቴ ይሆኑ ነበር። እንዲያውም ከእናቴ ጋር ይተዋወቁ ነበር። በወቅቱ ሴት ልጅ ኀላፊነትን ወስዳ አንድን ትምህርት ቤት በዚያ



መልኩ ማስተዳደር በእጅጉ የሚከብድ ነበር። እርሳቸው ግን አድርገውታል።" ብለዋል።

ሦስተኛ ምሳሌዬ የሚሏቸው ደግሞ "ሚስ ስዊን" የተባሉ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበሩበት ጊዜ ርእሰ መምህር የነበሩ ሴት መምህራቸውን ነው። "በእግዚአብሔር በጣም ትልቅ እምነት የነበራቸው ሴት ነበሩ። እኅቴ እዚያ ስትማር ሁልጊዜ ስለ እኔ ስትነግራቸው፣ "እዚህ ማምጣት አለብሽ" ብለው ከሄድሁ ጀምሮ በሕይወቴ ላይ ብዙ ጠቃሚ ሚና ተጫውተዋል።"

በመጨረሻም ሳይጠቀሱ የማይታለፉት ወሳኝ ሰው ደግሞ ባለቤታቸው እንደ ሆኑ ዶ/ር ጀምበር ያሥምሩበታል። ባለቤታቸው ከንቲባ ዶክተር ኃ/ጊዮርጊስ ወርቅነህ ይባላሉ፤ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ዶክተር ሲቪል መሐንዲስ ናቸው። በአገራችን ዘመናዊ መንገድ ግንባታ ላይ ጕልሕ ሚና የተጫወቱና በአንድ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ የነበሩ ታላቅ ሰው ነበሩ። ዶ/ር ኢንጂነር ኃ/ጊዮርጊስ ወርቅነህ ባደረባቸው ሕመም መስከረም 11 ቀን 1989 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። (የዶክተር ኃይለ ገዮርጊስ ወርቅነህን ሙሉ የሕይወት ታሪክና የሥራ ክዋኔ ለማወቅ በ1992 ዓ.ም የታተመውን «የሕይወቴ ታሪክ» የሚለውን መጽሐፍ ማንበብ ቤተ ሰቡ ያለፈበትን ውጣ ውረድ ለማየት ይጠቅማል።) "ባለቤቴም በእኔ ላይ ብዙ በጎ ተጽዕኖዎችን አሳድሯል። በሌላ በኩል ሥራ ሲሠራ አጥርቶ መሥራትና ድጋፍ መስጠት፣ ማበረታታት፣ ከበስተ ኋላዬ ሆኖ በራሴ መሥዋዕትነት የጀመርሁትን ሥራ እንድጨርስ ያደርግ ነበር። ባጭሩ በሕይወቴ ትልቅ ሚና ተጫውቷል።"

ዶ/ር ጀምበር ከአንድ እናትና አባት የተወለዱ ሦስት ወንድሞች፣ አንድ እኅት አሏቸው። "ታላቅ እህቴ ወደ ውጪ ስትወጣ ቤት ውስጥ ሴት ልጅ እኔ ብቻ ቀረሁ" የሚሉት ዶ/ር ጀንበር በቤተ ሰብ አስተዳደግ በኩል ምንም ዐይነት የጾታ ተጽዕኖ ሳይገጥማቸው እንዳደጉ ይናገራሉ። "ወንድሞቼ ለእኔ ድጋፍ ይሰጡኝ ነበር። የቀረሁት ሴት





አንድ እኔ ብቻ ነበርሁ። ሦስቱም ወንዶች ነበሩ። ትልቁ ወንድሜ ‹የእኛ አገር ሴቶች ቶሎ ስለሚያገቡ የእርሷ ተራ ይሁንና ትሂድ ብሎ እናቴ እኔን አስቀድማ ወደ ውጪ ለትምህርት እንድትልክ አግባባት። ስለዚህ በመካከላችን መተሳሰብና መደጋገፍ ነበር። ብዙ ጊዜ ወንድሞቼ በሴትነቴ ያበረታቱኛል።"

ዶ/ር ጀምበር በአጠቃላይ ስለ ወንድሞቻቸውና እኅቶቻቸቻቸው እንዲህ ይላሉ፤ "የእናቴ የመጀመሪያ ባል ከስደት ከማዳጋስካር ተመልሰው ዓመት እንደቈዩ ሞቱ። እርሳቸው ከሞቱ በኋላ እኛ ተማሪ ቤት ገብተን ራሳችንን እስክንችል ድረስ ለረዥም ጊዜ አላገባችም ነበር። ትልቅ ወንድሜና እኅቴ ሞተዋል። በጣም ብዙ ሚና የተጫወተ አንድ ታላቅ ወንድሜ እና ሌላ ታናሽ ወንድሜም አሉ። እናቴ ደግሞ ሌላ ባል አግብታ የወለደቻቸው ሦስት ልጆች ሲኖሩ፣ ሁለቱ አሜሪካ፣ አንዷ እዚሁ አለች።" ዶ/ር ጀምበር ከሚች ባለቤታቸው ሁለት ወንድና ሁለት ሴት ልጆች የወለዱ ሲሆን፣ አንዱ ልጃቸው ባለቤታቸው ባረፉበት ዕለት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷቸዋል። ሌሎቹ ልጆቻቸው ግን አሁን እየሠሩት ባሉት ሥራ ላይ ጕልሕ ሚና እየተጫወቱ እንደ ሆነ ተናግረዋል።

ዶ/ር ጀምበር እየሠሩ ካሉት «ከድኾችም የባሱ ድኾችን» የመርዳት ተግባር በተጨማሪ፣ "የእስረኛ መቅረዝ" የምትልና "በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ለሚኖሩ የሚታይ ይብርሃን ጭላንጭል" የሚል መጽሐፍ ጽፈው አሳትመዋል። የባለቤታቸውንም ግለ ታሪክ የያዘ መጽሐፍ ለሕትመት አብቅተዋል። ምንም እንኳ ባገለገሉባቸው መሥሪያ ቤቶች ያዩአቸው የነበሩትን ኢትሐዊነትና አድልዎ መታገላቸው ተገቢ እንደ ነበረ ቢያምኑም፣ ትግላቸውን በጥበብና በዘዴ ባለማድረጋቸው የሚጸጸቱበት እንደሆነና ከዚያም ብዙ ትምህርት እንደ ተማሩ ይናገራሉ። መስተካከል አለበት ብለው የሚያስቡትን ነገር ደግሞ እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል። "የመረዳዳት ባህላችን እጅግ በጣም ደካማ ነው። ድኻው ለድኻው ያለው አመለካከት ያሳዝናል። ያለው



ሰው ለሌለው አለማካፈሉም፣ አጥቶ ያገኘው ወደ ኋላ መለስ ብሎ የቀድሞ ማንነቱን አስታውሶ አሁን ተቸግረው ላሉ ሰዎች አለመራራቱም ያሳዝናል። ‹እኔ በዚህ አልፌ ነበርና ሊላው በዚህ በኩል አይለፍ ብሎ ቢናገር መልካም ነበር።"

## <u>መወድስ</u>

በተክለ ሃይማኖት በመርካቶ ጓሮ
ጀንበር ስታበራ ተሻሻለ ኑሮ





## <u>ትምህርተ ውልብታ</u>

ከመጻሕፍት የተማርነውንና ከውጭ አገር ያየነውን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋራ አጣጥመን መሥራት ።

በየተሰማራንበት የአገልግሎት መስክ የምናያቸውን ኢፍትሓዊነቶች ሁላችንም ኀላፊነት እየተሰማን በማስተዋልና በጥበብ ብንታገላቸው ሰብአዊና ዜግነታዊ ግዴታችንን በሚገባ እንወጣለን።

ጽናት ማለት፣ ቁልቁል በሚጋሽብ ውሃ ሽቅብ እየቀዘፉ እንደ መሄድ ያህል ነው። ልክ እንደዚሁ በሚያታግል የሕይወት ገጠመኝ «ይቻላል» ብሎ መቀጠል የጽናት ምልክት ነው።

ዶ/ር ጀንበር የርኅራኄና የትጋት ምሳሌ ሆነው እናያቸዋለን

ባሕር ቀድተን መጨረስ ባንችልም የኩሬ ውሃ መጨለፍ ትርጒም ሊሰጠን ይገባል።ያቅማችንን መሥራት።



## የውልብታ ምንጭ

ኃይለ ገዮርጊስ ወርቅነህ ኢንጅነር ዶክተር የሕይወቱ ታሪክ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት 1992 ዓ.ም አዲስ አበባ

ከዶክተር ጀምበር ተፈራ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ሚያዚያ 1999 ዓ.ም

ከወ/ሮ ዘነበወርቅ ብሥራት ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ሚያዚያ 1999 ዓ.ም

ከወ/ሮ ሐረገወይን ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ሚያዚያ 1999 ዓ.ም

Jember Tefera, *"Entering the world of poverty"* A Doctoral Thesis for the partial completion of Doctor of Ministry Program





## የአንባቢው የግል ማስታወሻ







# ፲፱



## ደበበ ሰይፉ
## 1942 – 1992
## ከዘመን ኩርፊያ

መጻሕፍትን አንብቡ፣ መግዛት ባትችሉ እንኳን ተውሳችሁ አንብቡ። ለማንበብ ከሆነ እስከ መስረቅም ዝለቁ። ግን አንብባችሁ ለባለቤቱ መልሱ፣ ደግሞ አንዲት ገጽ ከውስጡ አትቅደዱ፤ እና አንብቡ አንብቡ

ልጅነት በሚለው ግጥሙ <<አይ ያች የዘመን አምባ በብይ ድብደባ በኳስ ጥብጠባ>> ሲል የልጅነት ጊዜውን ተመልሶ የሚቃኘው የሥነ ጽሑፍ ተመራማሪ፣ ታዋቂ ገጣሚና ጸሐፊ ተውኔት ደበበ ሰይፉ ነው። የተወለደው በቀድሞው ሲዳሞ ክፍለ ሀገር፣ ይርጋለም ከተማ ከእናቱ ከወ/ሮ የማርያም ወርቅ አስፋውና ከአባቱ በጅሮንድ ሰይፉ አንተን ይሰጠኝ በሐምሌ 5 ቀን 1942 ዓ.ም. ነበር።

የመጀመሪያ ወንድ ልጅ በመሆኑ በወላጆቹ ዘንድ ልዩ እንክብካቤ ይደረግለት ነበር። በልጅነቱ እንደ እቻዎቹ ጨዋታ ወዳድ የነበረ ቢሆንም፣ በተለይ ለብይ ጨዋታ ያለው ፍቅር የላቀ ነበር። እናቱ እንደሚናገሩትም በዚሁ ጨዋታ ደበበን ማንም ችሎ የሚገጥመው አልነበረም። <<የመንደር ብይ በሙሉ እሱ ጋር ተሰብስቦ ይገባል። አባቱ ብይ ጨዋታን እንደ ነውር አድርገው ስለሚቈጥሩ የሰበሰበውን ብይ ድራሹን እንዳያጠፉበት የሚያደርገው ጥንቃቄ ልዩ ነበር። ደበበ ብይ በተጫወተበት ሁሉ መርታቱና ጠብ መነሣቱ አይቀርም፤ ስለዚህ ተከታዩ በሆነው በታችለ ሰይፉ ጋሻጃግሬነት ነው የሚንቀሳቀሰው>> እናቱም ጨምረው እንደሚናገሩት ደበበ ለብይ ጨዋታ ካለው ከፍተኛ ፍቅር የተነሣ ተቈንጥጧል፤ ተገርፏልም። ዳግም እንዳይጫወት ከተነገረው በኋላ እንኳ በድብቅ ይጫወት ነበር።

ገና ከልጅነቱ ፊደል ዕጣው የሆነ ጉበዝ ተማሪ ነበር። እናቱ እንደሚያስታውሱት ዳዊት ለመድገም ምንም ያህል አልወሰደበትም። አባቱ ከቄስ ትምህርት ቤት አውጥተው መደበኛ ትምህርት ቤት እንዲገባ ሲያደርጉት ልበ ብሩህነቱን አይተው እዚያው የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሊያደርጉት አስበው የነበሩት የኔታ በጣም አዘኑ።



አባቱ አዲስ አበባ ደርሰው ሲመለሱ መጻሕፍትና መጽሔቶች ገዝተው ይመጡ ስለ ነበር ይህ ለደበበ ገና ከልጅነቱ ከፍተኛ የማንበብ ፍቅር እንዲያድርበት አድርጓል። በተጨማሪም ቴያትርና ሌሎች ዝግጅቶች በሚኖሩ ጊዜ



ልጆቻቸውን ይዘው የመሄድ ልማድ ስለ ነበራቸው ይህም የቴያትር ፍቅር እንዲያድርበት ረድቷል። 4ኛ ክፍል ሳለ ከእኅትና ከወንድሞቹ ጋር መጋረጃ ጋርዶ ድራማ ለመሥራት ይሞክር ነበር። «ወ/ሮ ዓለም» ከሚል መጽሐፍ ላይ ወስዶ ተዋናዮችን ወስኖና መርጦ ለታላላቆቹ ድራማ ያሳይ እንደ ነበር እናቱ ይናገራሉ። ደበበ ከልጅነቱ ጀምሮ ከሰው ተገልሎ የመቀመጥ ልማድ ነበረው። ብቻውን ወራጅ ወንዝ እያየ መቀመጥ ያስደስተው ነበር። ቤተ ሰቦቹ እንደሚናገሩት ምንም እንኳ የደበበና የቤተ ሰቡ ግንኙነት ጥብቅና እጅግ የተቀራረበ ቢሆንም፣ የግሌ የሚለው፣ ብቻውን በተመስጦ ወይም በንባብ የሚያሳልፍበት ግዜ እጅግ ሰፊ ነበር። ከዩኒቨርሲቲ ተማሪነት ጀምሮ የቅርብ ጓደኛው የነበሩት አቶ ታምራት እጅጉ በአንድ ወቅት ስለ ደበበና ቤተ ሰቡ ግንኙነት በሰጡት አስተያየት ደግሞ <<ደበበ እነዚህን የልጅነት ጊዜዎች አውርቶ አይጠግባቸውም ነበር። ስለ ይርጋለምና የልጅነት ዘመኑ ሲያነሣ ብትሰማ ፈዘህ ትቀራለህ። ስሜቱ ይሞቃል>> ይላሉ። <<ይርጋለም>> በሚለው ግጥሙ ይህ ፍቅሩ ጐልቶ ሆኖ ይታያል፤ <<የልጅነቴ ሕልም ቀለም፣ ዐይኔን የከፈትሽው ጨረር ወርቃማዩቱ ጀምበር>> ሲል ያወድሳታል። የይርጋለምን አካባቢ ትእይንትና የልጅነት ትዝታዎቹን የሚያንጸባርቁት ግጥሞቹ «የብርሃን ፍቅር» በተሰኘው መጽሐፉ ውስጥ ይገኛሉ።

ደበበ ይርጋለም ከተማ «ራስ ደስታ» በሚባል ትምህርት ቤት የስምንተኛ ክፍል ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ቤተ ሰቡ ወደ አዲስ አበባ በመዛወራቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በኮከበ ጽባህ ትምህርት ቤት አጠናቀቀ። ቀጥሎም በቀድሞው የኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ለአንድ ዓመት ያህል የቢዝነስ ትምህርት ከተማረ በኋላ በትምህርቱ ባለመደሰቱ <<አእምሮን የማይቈነጥጥ ትምህርት>> በማለት ወደ አርትስ ፋኩልቲ ተዛውሮ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል በ1965 ዓ.ም. የሥነ ጽሑፍ የመጀመሪያ ዲግሪውን አገኘ። ከአምስት ዓመት በኋላም በዚሁ ዩኒቨርስቲ የማስተርስ ዲግሪውን በእንግሊዘኛ ሥነ ጽሑፍ



ያገኘ ሲሆን ውጤቱም የተዋጣለት እንደ ነበር የሚያውቁት ይመሰክራሉ።

ለሥነ ጽሑፍ የነበረው ፍቅር የጀመረው ገና ከልጅነቱ ነበር። የዚህ ብርዕ ወዳጅ ተማሪ የነበረው መሠረት አታላይ በ«ፈርጥ መጽሔት» ስለ እርሱ በጻፈው መጣጥፍ ገና ከልጅነቱ ባገኘው ነገር ላይ፣ በወዳደቀ ወረቀት፣ በጋዜጣ ቅዳጅ ሳይቀር ግጥም መጻፍ መውደዱን ገልጿል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ሆኖ ግጥሞች ይጽፍ ነበር። በምሥራች ሥነ ጽሑፍ ክፍል በተዘጋጀ የሥነ ጽሑፍ ውድድር «ዘላለም» የሚለው አጭር ልብ ወለድ ጽሑፉ አንደኛ ወጥቶ ከሌሎች የጸሐፍት ሥራዎች ጋር በአንድ ጥራዝ ታትሟል።

የማስተርስ ዲግሪውን በከፍተኛ የማዕረግ ነጥብ (በአራት ነጥብ በመመረቁ) በውጭ አገር ዩኒቨርስቲ የዶክትሬት ዲግሪውን እንዲቀጥል የሚያስችለው ቢሆንም ሳይቀጥል ቀርቷል። በርካታ የሥራ ባልደረቦቹ ትምህርቱን እንዲቀጥል ቢወተውቱትም በጄ አላለም። ለውትወታዎችም የሚሰጠው መልስ፦ <<መጽሐፌ የዶ/ር ደበበ ሰይፉ እንዲባል ነው? አሁን ያለሁበት ሁኔታ ብዙ ነገር እንድሠራ የሚያደርገኝ ነው>> ይል ነበር። ወንድሙ አቶ አበበ እንደሚናገሩት ማወቅና ዕውቀትን ማካበት የመፈለጉን ያህል ከዩኒቨርስቲ 2ኛ ዲግሪውን ካገኘና እዚያው ማስተማር ከጀመረ በኋላ ትልቅ ትኩረት የሰጠው ለተጨማሪ ትምህርት ሳይሆን የተማረውን በተግባር ለመተርጎም ወይም ያለውን ዕውቀት ለአገር ለወገን በማካፈል ላይ ነበር።

ደበበ በመጀመሪያ የሥነ ጽሑፍ ትምህርት ሲሰጥ ከቈየ በኋላ ከ1980 ዓ.ም ወዲህ ወደ ቲያትር ጥበባት የትምህርት ክፍል ተዛውሮ ማስተማር ቀጠለ። እርሱ ያስተማራቸው ተማሪዎች ብዙዎቹ ስላሳደረባቸው አዎንታዊ



ተጽዕኖ ይናገራሉ። ደበበ በርካታ ወጥና ትርጉም ተውኔቶች የጻፈ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ <<እናትና ልጆች>>፣ <<ከባህር የወጣ ዓሣ>>፣ <<እነሷና እነሱ>>፣ <<ሳይቋጠር ሲተረተር>>፣ <<የሕግን



ሽማግሌ>>፣ <<ክፍተት>>፣ <<ዕድምተኞቹ>> እና <<ጋሊዮ ጋሊሊ>> ይጠቀሳሉ። <<ክፍተት>> የተሰኘው የትርጉም ተውኔት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በተደጋጋሚ ታይቷል። ደበበ ለበርካታ ዓመታት የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር ሊቀ መንበር ሆኖ ከመሥራቱም ባሻገር «ብሌን» የተሰኘው የማኅበሩ መጽሔት አዘጋጅም ነበር። በተጨማሪም ቀድሞ «ኩራዝ» ተብሎ በሚታወቀው የኅትመት ድርጅት የቦርድ አባል ሆኖ ሠርቷል።

በቲያትር ጥበባት ክፍል ከ1981-1984 ዓ.ም. በሊቀ መንበርነት ባገለገለበት ወቅት ብዙ ለውጦች አድርጓል። በምርምር ረገድም በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ላይ በርካታ ምሁራዊ መጣጥፎችን በአማርኛና በእንግሊዝኛ አበርክቷል። ለዚህም ለማስተርስ ዲግሪው ያቀረበው የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚለው በዋናነት የሚጠቀስ ሲሆን በተጨማሪም እንደ መማሪያ መጽሐፍነት እያገለገለ ያለው «የቲያትር ጥበብ ከጸሐፌ ተውኔቱ አንጻር» የተሰኘው መጽሐፍ ሌው ተጠቃሽ ነው።

ደበበ በኢትዮጵያ ሬድዮ አማካሪና ረዳት አዘጋጅ፣ እንደዚሁም ተርጓሚ ነበር። ከፍተኛ የእንግሊዝኛ ችሎታ እንዲሁም መካከለኛ የፈረንሳይኛና የዐረብኛ ዕውቀት እንደ ነበረው የሚያውቁት ይመሰክሩለታል። ለአማርኛ ቋንቋ እድገት ከፍተኛ ቅናት የነበረው ደበበ በወቅቱ ለማርክሳዊና ለሙያዊ ሥነ ጽሑፍ እሳቤዎች የሚያስፈልጉ ስያሜ ቃላት *(Terminologies)* በመፍጠር ለቋንቋው እድገት የበኩሉን ድርሻ አበርክቷል። መሠረት አታላይ እንደሚናገሩት፣ ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር የውጭ ቋንቋ በቀጥታ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ እየቀላቀሉ መጠቀም በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ዶ/ር ፈቃደም «አማርኛን ስለማናውቀው ነው እንጂ ሰፊና ጥልቅ ቋንቋ ነው» የሚል አስተሳሰብ እንደ ነበረው ይናገራሉ። <<መቼት>>፣ <<ገጸ ባሕርይ>>እና <<ቧልታይ>> የመሳሰሉ የሙያ ቃላት የእርሱ ፈጠራ እንደ ሆኑ ይነገራል።



በተፈጥሮው ሰልቹ የነበረው ደበበ

ተደጋጋሚ ነገር ፈጽሞ አይወድም። በተለያዩ የሕይወት መደብ የሚገኙ ሰዎችና ታክሲ ሹፌሮች የሚናገሯቸውን ወጎች መስማት ያስደስተው ነበር፤ አዲስ ነገር እስከ ሆነ ድረስም ሳይሰለች ማዳመጥ ይችል ነበር። ደበበ እጅግ ሥራ ወዳድና ጠንካራ ሠራተኛ እንደ ነበር የሚያውቁት ሁሉ የሚመሰክሩለት ነው። <<ደበበ ጥብቅ ሥራ ከያዘ ሰው ማናገር ቀርቶ ማየት አይፈልግም>> ይላሉ አቶ አበበ፤ «በሥራ ሰዓቱ ለሚመጡ ሰዎች ይቅርታ አልነበረውም። ቀደም ብለው መጥተው እየተጫወቱ የሥራ ሠዓቱ ከደረሰ ተጫወቱ ብሎ መጻሕፍት ቤት ገብቶ ይዘጋል። አንዳንድ ሰዎች መጥተው እርሱን ሳያገኙ ተነሥተው የሚሄዱበት ጊዜም አለ።»

ለጽሑፍ ሥራው የሚመርጠው ሌሊቱን ነበር። ለተወሰነ ሰዓት በጊዜ ተኝቶ በመነሣት ሌሊቱን በሥራ ያሳልፋል። እስከ ንጋቱ ድረስ ይሠራል። ደራሲና ባልደረባው የነበረው መስፍን ሀብተ ማርያም እንዲህ ይላል፦ «በጣም ጠንካራ፣ ትጉህ ሠራተኛ ለተሰለፈበት ወደ ኋላ የማይል ነበር። በማስተማር ፈጣሪ /innovator/ ዐይነት ነበር። የምናስተምረውን ኮርስ እንዲህ ብናደርገው እያለ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንድናሻሽል በማድረግ በኩል ፊት መሪ ነበር።» ተማሪው የነበረው ነቢዩ ተካልኝም እንዲህ ሲል ይህን ሐሳብ ያጠናክራል፦ <<ሥራውን ይወዳል፣ ውጤታማም ነበር። ብዙ ጊዜ ኢንፎርማል [ቀለል ያለ] የሆነ ነገር ይወዳል። በራሱ መንገድ ነጻነት ይሰጠናል፣ ዲሞክራትም ነበር። ተማሪዎች ያከብሩታል። ጥሩ መምህር፣ ዐዋቂና ሊቀርቡት የሚችሉት ዐይነት ሰው ነበር።» አቶ አቦነህ አሻግሬ በበኩላቸው <<ደበበ በጣም ዐዋቂ ነው። ብዙ አንብቧል፤ ክፍል ገብቶ ሲያስተምር ብዙ ዕውቀት ያስተላልፋል። ተማሪዎቹ ይወዱታል፣ ከአንዳንድ ተማሪዎቹም ጋር የጓደኝነት ያህል ይቀራረብ ነበር።>>



ደበበ ሰፊና ጥልቅ ንባብ እንደ ነበረው በዙሪያው የነበሩ ሰዎች ሁሉ የሚመሰክሩለት ነው። የግጥምቹ ሐሳቦች ጥልቀትና ክብደት በሥነ ጽሑፍና በፍልስፍና የነበረውን ሰፊ ንባብ



ያመለክታሉ። መሠረት አታላይ የእርሱ ተማሪ ሳሉ አበክሮ የማንበብን ጠቀሜታ ለተማሪዎቹ ሁሉ ይነግራቸው እንደ ነበር ያስታውሳሉ። <<መጽሐፍት አንብቡ፣ መግዛት ባትችሉ እንኳ ተውሳችሁ አንብቡ። ለማንበብ ከሆነ እስከ መስረቅም ዘለቁ። ግን አንብባችሁ ለባለቤቱ መልሱ፣ ደግሞ እንዲት ገጽ ከውስጡ አትቅደዱ፤ እና አንብቡ አንብቡ ይል ነበር» ይላሉ። ወንድሙ አቶ አበበ የንባብ ምርጫው በአመዛኙ ቀደምትነት ያላቸው (ክላሲካል) የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች፣ ፍልስፍናና ታሪክ እንደ ነበር ያወሳሉ። ሲያነብ ጥናት እንደሚያካሂድ ዐይነት ነው የሚያነበው። ማንበብ ለደበበ ሕይወት ነው። ሞቻለሁ የሚለው ማንበብ የማይችልበትን ጊዜ ነው። የንባብ ፍጥነቱም የተመሰከረለት እንደ ነበር ጨምረው ይናገራሉ።

ደበበ ፈርጀ ብዙ ዝንባሌዎች ቢኖሩትም በአንባቢ ዘንድ በይበልጥ የሚታወቀው በገጣሚነቱ ነው። ግጥሞቹ <<ጽጌረዳ ብዕር>> በተባለ መድበል እንደዚሁም <<የብርሃን ፍቅር>> /1980/ እና <<ለራስ የተጻፈው ደብዳቤ>> /1992 /በሚሉ ቅጾች ታትመዋል። ግጥሞቹ በዩኒቨርስቲ ለአማርኛ ተማሪዎች መደበኛ ንባቦች ናቸው። ያልታተሙ ግጥሞችና ሌሎች ጽሑፎች እንዳሉትም ይነገራል።

ከፍተኛ የቋንቋ ክህሎትና ምጥቀት የሚንጸባረቅባቸው ግጥሞቹ በበርካታ አንባቢዎች ዘንድ አድናቆትን አትርፈውለታል። በማርክሳዊ አመለካከቱና የጋለ የአገር ፍቅሩ ሳቢያ ግጥሞቹ በአመዛኙ ማኅበራዊ ቅኝት አላቸው፤ ለሕዝብ ተቆርቋሪነቱ በበርካታ ግጥሞቹ ውስጥ ተንጸባርቋል። <<ሐዘንሽ አመመኝ>> እና <<ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ>> በተሰኙ ግጥሞቹ 1966 ዓ.ም. ለተከሠተው ድርቅ መንግሥት ያሳየውን ግድየለሽነት በተባ ብርዕ በመኰነን በጥልቅ ስሜት የድርቁን ሰቈቃና ያስከተለውን አስፈሪ ውድመት ሥሎልናል። የአገር ውድቀትና የሕዝብ መራቈት ደንታ በማይሰጣቸው ምሁራንም ላይ ብርቱ ነቀፌታ ይሰነዝርባቸዋል። የግጥም ጥበብና ጥልቀቱን በተመለከተ በርካታ ሐያስያን አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። መስፍን



ሀብተ ማርያም እንዲህ ሲል አስተያየቱን ይሰጣል፡- «...ስሜትን ወጥሮ ለመያዝ ቍጥብና ውጥር ባለ ሁኔታ በምርጥ ቃላት ደማቅ ምስል መፍጠር የደበበ መልካም ተስጥዎ ነው። ቃላቱ በወጉ ተፈልገው በአስፈላጊው ቦታ በአስፈለገው ምስል የሚውሉ ናቸው። ከቶም አይንዛዙም፤ መንዛዛት ሲፈጥሩ፣ ከቶ ትርፍ ሲሆኑም አይቃጣቸውም። ታዲያ በቍጥብ አቀራረባቸው የሚፈጥሩት ምስል ግኡዙን ነፍስ ያለው የሚያስመል ነው።»

ኮሎኔል ሊቁ ዓለሙ የደበበ ግጥም የሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅንን በጎ ተጽእኖ እንደሚያመለክት ሲናገሩም፦ «አስታውሳለሁ ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን ግጥሞቹን ሲያነቡለት በደስታ የሚፈነድቀው፣ ጥሩወርቅ ዋቀዮ እና ደበበ ሰይፉ ሲያሰሙት ነበር። 'ውስጤን ነው የምታነቡልኝ ' ይላቸው ነበር። የደበበ ሰይፉ ገጣሚነት በተፈጥሮ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የጸጋዬ ገብረ መድኅን በጎ ተጽእኖም ያለበት ይመስለኛል። »

ደበበ በሕይወቱ መጨረሻ በሕመም መሠቃየት ስለ ጀመረ የማስተማር ሥራውን በቅጡ ማከናወን አልቻለም። ተክቶ ታደሰ የተባለ ሰው በመመረቂያ ጽሑፉ እንዳመለከተው በመገጣጠሚያ አካላት አለመታዘዝ ምክንያት ከዩኒቨርስቲ የማስተማር ሥራው ራሱን አሰናበተ።

ደራሲው ለ8 ዓመታት ያህል በጠና ከታመመ በኋላ ሚያዝያ 16 ቀን 1992 ዓ.ም በ50 ዓመቱ ዐረፈ። የቀብሩ ሥነ ሥርዓት የተፈጸመው በቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ሐውልቱ ላይ «ለራስ የተጻፈ» ድብዳቤ በተሰኘው መጽሐፉ ውስጥ የሚገኘው የሚከተለው ግጥሙ ተጽፏል፡-

ለምን ሞተ ቢሉ
ነገሩ ለሁሉ ሳትደብቁ ከቶ
ከዘመን ተኳርፎ
ከዘመን ተጣልቶ።






## መወድስ

ገለል በልና አንዴ ደግሞ ጫረው
የልብህን እሳት ለሰው ልጅ ንገረው
ለራስህ ደብዳቤ ከራስህ ጻፍና
የብርሃን ፍቅር ያብራ ያንተ ፋና

## ትምህርት ውልብታ

**ከፍተኛ ትምህርቱን ሊቀጥል ቢችልም እንኳ ያለውን ዕውቀት ለኅብረተሰቡ ለማዋል ይበቃል ማለትን በማወቅ በደረሰበት ደረጃ ኅብረተሰቡን ለማገልገል መወሰኑ**





## የውልብታ ምንጭ

Reuidlf Knut Molvaer "*Dabbaba Seifu*" in Encyclo pedia Aethooica Vol 2 P.4

——————"*Afewerq Yohannis and Debbebe Seifu, Notes on Ethiopian Writers of the late Twentieth century*" Northeast African Studies 6,3 1999

ፈርጥ መጽሔት መሠረት አታላይ ደበበ ሰይፉ፣ ለኪነ ጥበብ ተፈጥሮ ለኪነ ጥበብ የሞተ ሐምሌ 1992 ዓ.ም.

ፈርጥ መጽሔት ገጣሚ ደበበ ሰይፉ እንዴት ኖሮ ሞተ? ግንቦት 1993 ዓ.ም.

ተክቶ ታደሰ የደራሲ ደበበ ሰይፉ ሕይወት ታሪክና የሥነ ጽሑፍ ሥራው ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ /የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል 1993 ዓ.ም.





## የአንባቢው የግል ማስታወሻ









# ፳



## ደራርቱ ቱሉ
## 1964 –
## ቀድማ የበራች ኮከብ

«ሰዎች በየትም ቦታ ላይ የተለየ አክብሮትና አቀባበል ያደርጉልኝ ጀመር። በወሳኝ ቦታዎች ላይ ከታላላቅ ሰዎች ጋር የምገናኝ ሰው ሆንሁኝ። ያኔ ለአገሬ አንድ ወሳኝ ነገር ማድረጌ በትክክል ተቀረጸብኝ»

ዓመታት ዓመታትን ቢተኩ በማንኛውም መልኩ፣ መቼም ጊዜ የማይዘነጋ የታሪክ ምዕራፍ የጻፈች ፍልቅልቅ ኮከብ። ደራርቱ ቱሉ ለኢትዮጵያ ብሎም ለመላው አፍሪካ አትሌቲክስ እናት ለመባል የበቃችበትን አኩሪ የተግባር አሻራ ለመተው የቻለች፣ ቀድማ የበራች ኮከብ ናት።

አረንጓዴው ጐርፍ ተብሎ የተሰየመው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቡድን የዓለም ሩጫ አደባባዮችን በድል ከማጥለቅለቁ አስቀድሞ የቀዳሚነቱን ችቦ ደርሰው የለኮሱ ጀግኖች ስማቸው ደመቅ ብሎ ይጻፋል። አበበ ቢቂላ፣ ማሞ ወልዴ፣ ምሩፅ ይፍጠርና ሌሎችም። በብርሃን አለን ባዮቹ አገራት «ጨለማዋ አህጉር» ብለው የሚጠሯትን አፍሪካን ብርሃናዊ ገጽታ በአንጸባራቂ ድሎች እንዳሳዩ ሁሉ፣ በሴቶችም ያንን የወጤታማነት ጎሕ የቀደደች አትሌት የተገኘችው ከአፍሪካዊቷ ኢትዮጵያ ነው።

ከደራርቱ ትዝታ ጋር ለአፍሪካ፣ ለኢትዮጵያና ለራሷ ለደራርቱ የማትዘነጋ ወደ ሆነችው የስሜናዊቱ ስፔን ባርሴሎና ከተማ እንመለስ። ዘመኑ እንደ ኢትዮጵያውያን ዘመን አቈጣጠር 1984 ዓ. ም. ነው። የዛሬዋ አፍሪካና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ እናት ደራርቱ ቱሉ ወደ ባርሴሎና ኦሎምፒክ መንደር ስታመራ፣ ስለ ውድድሩ ታላቅነትም ሆነ ከዚያ በኋላ ስለሚከተሉት ውጤቶች አልተጨነቀችም። «ለኦሎምፒክ ብዙ ትኩረት አልሰጠሁም። ውድድሩን እንደ ማንኛውም ውድድር ነበር የተመለከትሁት» ስትልም ትዝታዋን ታስታውሳለች። የዓለም መገናኛ ብዙኃን በታላቁ የባርሴሎና ኦሎምፒክ የ10ሺህ ሜትር ርቀት ሩጫ የአሸናፊነቱን ግምት ለደቡብ አፍሪካዊቷ ኤሊና ሜየር ብቻ ሰጡ። በዚህ ግምታቸውም ፍጹም ጥርጣሬ አልነበራቸውም። ከአፍሪካ አህጉር የምትፈካ ጥቁር ኮከብ ትከሠታለች ብለው የጠበቁ አልነበሩም። በርግጥም በባርሴሎና፣ በታላቁ ኦሎምፒክ መድረክ የ10ሺህ ሜትር ርቀት ቀሪ አሥር ዙሮች ላይ ብዙዎች እንደ ጠበቁት ደቡብ አፍሪካዊቷ ኤሊና ሜየር 4900 ሜትር ሲቀር ሌሎችን ተወዳዳሪዎች ወደ ኋላ በማድረግ ተንጥላ ወደ ፊት እየመራች ወጣች። ዳሩ ምን





ያደርጋል ከግምት ውጪ የነበረችው ሌላ ጥቁር ኮከብ እግር በእግር ተከተለቻት። ደራርቱ ኤሊናን በወቅቱ የተከተለችው፣ «የአሠልጣኞቼን ምክር ለመተግበር ነበር» በማለት ትውስታዋን ትናገራለች። በዚህም የደራርቱን አሠልጣኞች የድል ባለ ርእይነት ማየት ይቻላል። መጨረሻው የሩጫ ዙር ደረሰ። የደራርቱ ቀጫጭን እግሮች ተአምራዊ ፍጥነት አሳዩ። የወጣቷ ኢትዮጵያዊት እግሮች የባርሴሎናን የመሮጫ ትራክ በርግጠኛ የድል ስሜት እየረገጡ ወደ ፊት ሲገሠግሡ የብዙ ኢትዮጵያውያን ዐይኖች በጒጒት እንባ ተሞሉ፣ የአረንጓዴው ጐርፍ ቡድን አፍቃርያን ልብ ሁሉ በደስታ ከተለመደው ሁደት በላይ መደለቅ ጀመረ። ደራርቱን ያላሰቡና ግምት ያልሰጧት ዜጎችም በትኩረት ቀጫጭን እግሮቿንና በልበ ሙሉነት የታጀበውን ፍጥነቷን ከማንነቷ ጋር አጣምረው ለማወቅ በጒጒት እርሷ ላይ አፈጠጡ። በባርሴሎና ኦሎምፒክ ደራርቱ ቱሉ የአሸናፊነቱን መሥመር ቀድማ ረገጠች። ደራርቱ ደመቀች ኤሊና ደበዘዘች። አዲስ የተሰፋ ታሪክም ተጻፈ። «ከሰሃራ በታች ካሉ አገሮች በታላቁና በአስቸጋሪው የኦሎምፒክ ውድድር ወርቅ ለመውሰድ የመጀመሪያዋ ለመሆን የበቃች ፋና ወጊ ሴት አትሌት» ሆነች። ከዚህም የተነሣ እስከ አሁን ድረስ በብዙዎች ዘንድ የአፍሪካ የስፖርቱ ዓለም ቀዳሚት እመቤት እንደሆነች ትቈጠራለች። ይህንን ስፖርታዊ ድል የተጐናጸፈችው ቀዳሚት ኮከብ የት ተወለደች? እንዴትስ ወደ ሩጫው ስፖርት ገባች?

ደራርቱ የኢትዮጵያን አትሌቲክስ ውጤት ያሳመሩ በርካታ ጀግኖች በወጡበት የኦሮሚያ ክልል፣ በአርሲ ዞን ማሕደረ አትሌት በሆነችው እንደነ «አንበሳው ቀነኒሳ» እና በ «ይቻላል» መርሕ ባለ ድልነቱን ለረጅም ዓመታት ያስመሰከረው አትሌት ኀይሌ ገብረ ሥላሴ ዓይነቶችን ባፈራችው በበቆጂ ከተማ በ1964 ዓ.ም ተወለደች። ሰፊ ሊባል በሚችል ቤተ ሰብ ውስጥ ማደጓን ደራርቱ ትናገራለች። አሥራ ሁለት ልጆች ባሉበት ቤተ ሰብ ለእናቷ አራተኛ፣ ለአባቷ ደግሞ ዘጠነኛ ልጅ ሆና አደገች። የደራርቱ እድገት በአገራቱ



የገጠር አካባቢዎች ከሚያድጉ ሴት ልጆች አስተዳደግ የተለየ ስላልነበረ፣ በቤትም በውጪም በርካታ ሥራዎችን ታከናውን ነበር። የብዙ የገጠር ሴቶች ግዴታ ሆኖ የሚታየውን በጎችን የመጠበቅ፣ ከብቶችን የማገድ በእጅም የመፍጨትን ከባድ ሥራ እንዳደገችበትና ይህም እጅግ ፈታኝ የሆነ መንገድ ለዛሬ ታላቅነቷ መሠረት እንደ ጣለላት ትናገራለች። እንደ ማናቸውም የገጠር አካባቢ ልጆች ለመማርም አስቸጋሪ ሁኔታ አጋጥሚታል። በቤተ ሰቡ ውስጥ በርካታ ልጆች ስለ ነበሩ፣ ከነበረውም አስቸጋሪ ሁኔታ የተነሣ ደራርቱ ወደ ትምህርት ቤት ለመሔድ ከጓደኞቿ በሁለት ዓመት ጊዜ ለመዘግየት ተገዳለች።

ቀድሞ የበራችው ኮከብ አትሌት ትምህርት ቤት ገብታ ትምህርት ከመማሯ አስቀድሞ የሕይወትን 'ሀ ሁ' በብዙ ውጣ ውረድ ካለፋት እናቷ ብዙ ነገር መማሯን ስትገልጽ፦ «እናቴ ለእድገታችን ቍልፍ ሚና ተጫውታለች። ምንም እንኳ አባቴ እኛን የማሳደጉን ችግር ባይጋፈጥም፣ ለእርሱም ፍቅር አለኝ። ነፍሱን ይማረውና በቤት ውስጥ የሚበላ ነገር ካልጠፋ በቀር ስለ ማንኛችንም በሌላ ጉዳይ አይጨነቅም ነበር» ትላለች።

የአዳጊዋ ተማሪ የዕለት ተዕለት ኑሮ አእምሮን በትምህርት ለማጐልበትና ለማነጽ፣ በትምህርት ቤት አርፍዶ ላለመገኘትም በሚደረግ ሩጫ ተሞላ። የደራርቱ ለጋ እግሮች የቤት ውስጥ ግዴታቸውን ለመወጣት የሚችሉትን ሁሉ አድርገው ወደ ትምህርት ቤት ደግሞ ቢሮጡም፣ ከትምህርት ቤት የአርፋጅነት ቅጣት የማያመልጡበት ጊዜ በርካታ ነበር። ከአርፋጅነት ቅጣት ለማምለጥ በሚደረግ የዕለት ተዕለት የሩጫ ትንቅንቅ መሀል ግን የደራርቱ እግሮች የወደ ፊቱን ድል የሚወልድ ብቃትን መቋጠር ጀመሩ።



የደራርቱ የሯጭነት ምስጢር መገለጥ የጀመረው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቷ ውስጥ ነው። የወቅቱ የስፖርት መምህሯ ባዘጋጁት የአጭር ርቀት ሩጫ (400 ሜትር) ላይ በማሸነፍ



ወደ ውድድር ዓለም ገባች። በወቅቱ በየትኛውም ደረጃ ላይ መሮጥ ለሴት ልጆች አስቸጋሪ ቢሆንም የደራርቱ እግሮች የባህልና የማኅበረ ሰብ ተጽዕኖዎችን ሰብረው መውጣት ጀመሩ። በትምህርት ቤት ውድድሮች ላይ ትንሽ የአሸናፊነት ብልጭታን ያሳዩት የአዳጊዋ ጉልባች እግሮች ወደ ሆኑ የወረዳዎች ውድድር ተራመዱ። በተካፈለችባቸው የ800 እና የ1500 ሜትር ውድድሮች አሸነፈች። እነዚያ ድሎች ደግሞ ደራርቱን ወደ ኢትዮጵያ ዋና ከተማ ወደ አዲስ አበባ ውድድሮች ለመምጣት መንጠሪያ ሆኗት። አዲስ አበባም ላይ ተገቢ ልምድ ያልነበራት አትሌት በሁለቱ ርቀቶች ላይ የሦስተኛነትን ደረጃ አገኘች። ከደራርቱ ትንንሽ እግሮች ውስጥ በቅሎ የሚያድግ የድል ችግኝን አስቀድመው የማየት ኀይል ያላቸው በርካታ ክለቦች አትሌቷን በአዲስ አበባ ለማስቀረት ጥረት ማድረጋቸውን ቀጠሉ።

በርካታ ክለቦች ቢጎመጁትም፣ የደራርቱ ልብ ወደ ትውልድ መንደሯ፣ ወደ እናቷ ቍጣ ተጓዘ። «እናቴ በሩጫ ጊዜዬ እንዲጠፋ አትፈቅድም ነበር። እንደሚታወቀው በገጠራማ አካባቢዎች ሴት ልጆች ነጻነት የላቸውም። እናም ራሴን የምችልበት ሌላ መንገድ እንጂ መሮጡ አይደገፍም ነበር» ትላለች።

ደራርቱ የቤተ ሰቧን ጫና ተቋቁማ ሩጫውን ሙያ ብላ እንድትይዝ ያስገደዳት ክሥተት፣ በኢትዮጵያ አገር አቋራጭ ሻምፒዮና ላይ ማሸነፏን ተከትሎ ለማረሚያ ቤቶች ስፖርት ክለብ መፈረሚ ነው። በእንዲህ ዓይነት የታሪክ ጕዞ ወደ ማረሚያ ስፖርት ክለብ ስትገባ የ17 ዓመት ወጣት ነበረች። አሁንም ቢሆን በሻለቃነት ማዕረግና በሙሉ ጊዜ አትሌትነት የማረሚያ ቤቶች ፖሊስ ባልደረባ ነች። በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ ውድድሮችን እያደረገች በውጤቷ መሠረት ቀጥላ የመጀመሪያ ውድድሯን በኖርዌይ ስታቫንገር ከተማ ባለ ስድስት ኪሎ ሜትር ውድድር አከናወነች። ያስመዘገበችው ውጤት 23ኛነት ነበር። ይኼን ጊዜ ባለ እምቅ ድሏ ደራርቱም ሆነች አሠልጣኞቿ የደራርቱን አትሌትነት ዐፈር ቢያለብሱት ኖሮ በደራርቱ አማካይነት



የአፍሪካዊቱ ኢትዮጵያ ባንዲራ በዓለማችን ልዩ ልዩ ታላላቅ አገሮች መውለብለቡ ምኞት ሆኖ ይቀር ነበር። ነገር ግን ፍልቅልቂ ኮከብ በዚህ ውጤት ተስፋ ሳትቈርጥ በመጀመሪያ ደረጃ ከዓመት በኋላ ይህንኑ ውድድር በወርቅ ሜዳሊያ አኳኳሰችው። ወዲያውኑ ከባርሴሎና ኦሎምፒክ የጀመረ፣ ለሁለት አሥርት ዓመታት የዘለቀ የበላይነትን ያስመሰከረ ታሪክን ወደ ማስመዝገብ ተሸጋገረች።

በዐለም አቀፉ የአትሌቲክስ ፌደሬሽን ማኅበር እ.ኤ.አ. በ2006 የዓመቱ ኮከብ አሠልጣኝ ተብለው የተሰየሙት ዶ/ር ወልዴ መስቀል ኮስትሬ የተናገሩትን *Runner's World Marathon New York City* የተሰኘ አንድ የስፖርት ጋዜጣ እንደ ዘገበው፣ «በባርሴሎናው ውድድር እስከምታሸንፍ ድረስ እንዴት ያለች ጅግና እንደ ሆነች በደንብ አልተገነዘብንም ነበር» አትሌት ደራርቱ በዚሁ ጋዜጣ ላይ በሰጠችው አስተያየት እንደምትናገረው ደግሞ ለኢትዮጵያውያን አትሌቶች ድል ዋነኛው ምክንያት ዶ/ር ወልደ መስቀል ናቸው። እሳቸው «በልምምድ ጊዜ የምታደርጉት ብቻውን አይበቃም ከዚያ በላይ ውጤት ማምጣት የምትችሉ ናችሁ» ይሉናል። ደግሞም ለብዙ ድል መሠረት ጣይ መሆናቸውን ስትናገር «ከእርሳቸው በኋላ ማንም ቢያሠለጥነን የሚከተለው የእርሳቸውን እቅድ ነው አክላም ስትናገር እርሳቸው ለእኛ እንደ አባት ሆነው ሥርዓትንም ያስተምሩናል» ትላለች። በምትሰጣቸው የጋዜጣ ቃለ መጠይቅ መልሶች በአብዛኛው ከራሷ ይልቅ ስለሌሎች ጉብዝና መናገር የምትመርጥ መሆኗን መመልከት አዳጋች አይደለም። ለዚህም እንደ ተጨማሪ እብነት ወደ ሩጫው አትሌቲክስ ለመግባት መነሣሣት የፈጠረችባትና በሕይወት ዘመኗ የምታደንቃት የአትላንታ ኦሊምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት የሆነችው አትሌት ፋጡማ ሮባ እንደ ሆነች ትናገራለች።



ከፊቷ ፈገግታ ፍጹም አይጠፋም። በጊዜው ጽዮንና ሩት የምትላቸው የሁለት ሴቶች ልጆች እናት የሆነችው ደራርቱ የብዙ ሴት አትሌቶች እናትም ናት። የዓለማችንን የቀዳሚ ግምት



ትኩረት በሚያሸንፈው የኦሎሚፒክ ውድድር ላይ በአሥር ሺህ ሜትር የሁለት ጊዜ የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ ናት። በዓለም አገር አቋራጭ ሻምፒዮና ላይም ለሦስት ጊዜያት ያህል የድል ባለቤት ለመሆን በቅታለች። ደራርቱ የእርሷን አርአያነት ተከትለው ለወጡ በርካታ ኢትዮጵያውያት አትሌቶች ፈር የቀደደች፣ ዘመንና ሕዝብ የማይረሳት አትሌት ናት። የኢትዮጵያን የኦሎምፒክ እንቅስቃሴን የሚዘክር መጽሔት የደራርቱን በሩጫው ዓለም መነሣት «ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ የሴቶች የረጅም ርቀት ሩጫ ሂደት ላይ የለውጥ አሻራውን ያሳረፈ ክሥተት» ሲል ገልጾታል።

ከደራርቱ የባርሴሎና ድል በኋላ የሌሎች አህጉራት ዜጎች ልክ አበበ ቢቂላ በባዶ እግሩ ሮጠ ሮም ላይ በማራቶን ድል ያስገረማቸውን ያህል፣ በድጋሚ በአፍሪካ ውስጥ ከድኻ አገሮች የሚፈልቁ ውድና ብሩህ አትሌቶች እንዳሉ እንዲያስቡ አደረገ። በአፍሪካ በተለይም በኢትዮጵያ የሚገኙ የበርካታ ወጣት ሴቶችን የሩጫ ሕይወት መሥመር የሚያስተካክል መንገድ እንደሚሆን ግንዛቤ ማስገኘት አስቻለ። ከዚያ በኋላ ፋጡማ ሮባ አትላንታ ላይ የኢትዮጵያን የሴቶች የማራቶን ድል አስመዘገበች። ቀጥለውም መሠረት፣ ጥሩነሽ፣ እጅጋየሁ፣ ብርሃኔ ወርቅነሽና የመሳሰሉ ሴት አትሌቶች የሩጫ የኀይል ሚዛን ወደ ምሥራቅ አፍሪካዊቷ አገር ወደ ኢትዮጵያችን እንዲያጋድል አደረጉ። የዚህን ሁሉ ድል መሠረት በማስቀመጥ ደግሞ «የአንበሲት ድርሻ» የምትወስደው ደራርቱ ናት። ከበርካታ ዓለም አቀፋዊ ድሎቿ ባሻገር በዚህ ሕያው ሥራዋ ብቻ «ከኮከቦች በላይ ደምቃ የምትበራ ኮከብ ትሆናለች» በማለትም ደራርቱን በርካታ የድረ ገጽ ጸሐፊዎች አወድሰዋታል። ደራርቱ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ስፖርት ለዋለችው ውለታ ተጨማሪ ማስረጃ የሆነች የማትደበዝዝ ኮከብ ናት።



ከደራርቱ የኦሎምፒክ ድል በኋላ ሩጫ የወንድ ልጆች መገለጫ ብቻ መሆኑ ቀረ። ቀድሞ ከወንድ ልጆች ጋር ሲሮጡ አላስፈላጊ ስም

ይሰጣቸው የነበሩት ሴት ልጆች ሁሉ በሩጫ ሜዳዎች ብቅ ብቅ ማለት ሲጀምሩ 'ደራርቱ' የሚል ቅጽል ስም ይሰጣቸው ጀመር። የደራርቱ ስም የአሸናፊነትና የታላቅ ክብር መገለጫ ሆነ። በደራርቱ አገር መኮራት ሲጀምር፣ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እርሷን ለማወደስ ሲነሡ፣ ያን ጊዜ ደራርቱ ድል ተጐናጽፋ የተቀበለችው የኦሎምፒክ ወርቅ እጅግ ከፍተኛ ትርጕም እንዳለው ማመን ጀመረች። «ሰዎች በየትም ቦታ ላይ የተለየ አክብሮትና አቀባበል ያደርጉልኝ ጀመር። በወሳኝ ቦታዎች ላይ ከታላላቅ ሰዎች ጋር የምገናኝ ሰው ሆንሁኝ። ያኔ ለአገሬ አንድ ወሳኝ ነገር ማድረጌ በትክክል ተቀረጸብኝ» በማለት ደራርቱ የባርሴሎና ድሏን በስተኋላ ላይ የተገነዘበችበትን መንገድ ትገልጸዋለች።

ደራርቱ ከባርሴሎና አሸናፊነቷ በላይ ልዩ የሚያደርጋት ነገርም አለ። የበርካታ የስፖርቱ ዓለም አትሌቶች አሸናፊነት እንደ ብልጭ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ድርግም በሚል ክሥተትም ይሞላል። ሁለት አሥርት ዓመታት በተለያዩ የአትሌቲክስ ውድድር መድረኮች ያሳለፈችው ደራርቱ ግን የእህልቆትና የጽናት፣ የማይናጋ ውጤታማነትም ባለቤት ናት። በጕዳት ምክንያት ከውድድሮች ለረጅም ጊዜያት የራቀችባቸው አጋጣሚዎች ቢኖሩም ከአሸናፊነት አላስተጓጐላትም። ልጅ መውለድ ለእንደዚህ ዐይነቱ እንቅስቃሴ ፈተና ሆኖ ቢቈጠርም እናትነትን ከውጤታማነት ጋር አጣምራ መዝለቅ ችላለች።

እንደ ደራርቱ ዓይነት ስኬታማ አትሌቶች በሩጫ ዘመናቸው የማይረሷቸው አሳዛኝ የውድድር ጊዜያትና ውጤቶችም በጭራሽ አይጠፉም። በባርሴሎና ኦሎምፒክ ሳትጨናነቅ ያሸነፈችው ደራርቱ ከአራት ዓመታት በኋላ ከኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ቡድን ጋር ያመራችው ወደ አትላንታ ነበር ። አትላንታ ላይ እንደ ባርሴሎናው አልተዘናጋችም። በኦሎምፒክ የማሸነፍ ምንነት ግልጽ ብሎ ታውቋታል። ስለሆነም እ.ኤ.አ. በ1996 ወደ አትላንታ ስትጓዝ እንደ ባርሴሎናው ለኦሎምፒክ ባይተዋር



አልሆነችም። የተጓዘችው በርካቶች ትኵረታቸውን አሳርፈውባት ነበር። በአትላንታ ግን ደራርቱና ሻምፒዮንነት ተራራቁ።



የተዘጋጀችውን ያህል ውጤት ማስመዝገብ ተሳናት። ደራርቱ «አትላንታ ለእኔ መራር የኦሎምፒክ ትውስታ ነው። የሚገባኝን ያህል ብዘጋጅም ውድድሩ ሲቃረብ መታመሜ መጨረሻው እንዲበላሽ አድርጎብኛል» ስትልም በቍጭት ትናገራለች።

የደራርቱ ልጅ ጽዮን የተወለደችው በኢትዮጵያውያን ዘመን አቈጣጠር 1990 ዓ. ም. ላይ ሲሆን ደራርቱ ከጽዮን መወለድ በኋላ በእናትነትና በምትወደው ስፖርት ውስጥ በትግል የተሞላ ሕይወትን መምራት ቀጠለች። በተለይ ደግሞ የአትላንታውን መጥፎ አሻራ ለማጥፋት ስትል እልህ የተሞላበት እንቅስቃሴዋን አጠናከረች። ከሁለት ዓመታት የእናትነት ቈይታ በኋላ ወደ ትራክ ውድድር ብትመለስም፣ በርካታ የአትሌቲክስ ስፖርት አፍቃሪያን ደራርቱን እንደገና አሸናፊ ሆና እናያታለን ብለው ለማሰብ አልደፈሩም። ያልተጠበቀው እንዲሆን በማድረግ ለአትሌቲክስ ስፖርት አፍቃሪዎች አዲስ ክሥተትን ማሳየት ልማዷ የሆነው ፍልቅልቅ ኮከብ ግን እንደገና ዓለም የሚነጋገርበትን የጀግንነት ገድል ፈጸመች። ደራርቱ ሲድኒ ኦሎምፒክ ላይ በ10 ሺህ ሜትር ለኢትዮጵያ፣ ለአፍሪካና ለእራሷ የወርቅ ሜዳሊያ አስገኘች። ፍልቅልቋ ኮከብ፣ ግቡ ክንዷ ላይ ፊጽሞ የማይጠፋው ጀግና አትሌት በሲድኒ አደባባይ የአገሯ መዝሙር ሲዘመርና ባንዲራዋ ሲውለበለብ እንባ በጕንጮቿ ላይ መንከባለል ጀመረ። ብዙ ተተኪ አትሌቶችን ያጀገኑ የእንባ እንክብሎች ከደራርቱ ፊት ላይ ተከታትለው ወረዱ። አፍሪካውያን ኢትዮጵያውያን መቼም የማይዘነጉት ትዕይንት ነበር ማለት ይቻላል። ደራርቱ የሲዲኒ ኦሎምፒክ ድሏን፣ «አትላንታ ላይ የደበዘዘውን የስሜቴን ገጽታ የቀየረ ታላቅ ክሥተት» በማለት ገልጻዋለች።

ደራርቱ ቱሉ ከኢትዮጵያ የኦሎምፒክ ልኡካን ቡድን አባላት ጋር በመኾኑት ወደ ሲድኒ ስትጓዝ ጕዞዋ ለተሳትፎ ብቻ ይሆናል ያሉ ሁሉ ግምት ብቻ ሆነው ቀሩ። ልጅ ወልዳ መኖሟ፣ እድሜዋም እየገፋ መምጣቱን ምክንያት



በማድረግ ለደራርቱ ዝቅተኛ ግምት የሰጡ አንደበቶች ሁሉ ተዘጉ። ኢትዮጵያ በኦሎምፒክ የተሳተፎ ታሪኳ ሲድኒ ላይ ከፍተኛውን ውጤት ስታስመዘግብ የቀዳሚዋ ኮከብ ድርሻ እጅግ የላቀ ሆነ። ከሲድኒ በኋላም በካናዳ ኤድመንተን የሚያስገርም የ10 ሺህ ሜትር የሩጫ ፉክክር ታየ። በዚህ ውድድር ላይ የአንድ አገር ልጆች ደራርቱና ብርሃኔ በስፖርቱ ታሪክ የማይዘነጋና እልህ አስጨራሽ ፉክክርን አሳዩ። ነገር ግን የመጨረሻውን መሥመር ልማደኛዋ ባለ ድል ደራርቱ ቀድማ ረግጣ ገባች፤ ኮከቢቱ እንደገና ደመቀች!

በ1990ዎቹ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ የ10 ሺህ ሜትር ርቀት «ንግሥት ደራርቱ ቱሉ» ለረጅም ዓመታት የርቀቱን የበላይነት ይዛ ብትቈይም ቀስ በቀስ ቦታውን ራሷ መነቃቃትን ለፈጠረችባቸው የስፖርቱ ተተኪ ባለ አደራዎች አሥረከበች። እርሷ ፊቷን ወደ ማራቶን ስታዞር በ10 ሺህ ሜትር ርቀት ላይ ጥሩነሽና መሠረት ነገሡ።

ደራርቱ በኦሎምፒክ ላይ በ10,000 ሜትር ርቀት ሁለት የወርቅ ሜዳሊያ በማግኘት በዓለም ብቸኛዋ አትሌት ናት። በአትሌቲክስ ስፖርት ስኬቷ በኦሎምፒክና በዓለም ሻምፒዮና ላይ ስድስት የወርቅ ሜዳሊያን አግኝታለች። ከሀያ ዓመታት በላይ ያለማቋረጥ በመሮጥም ደራርቱ የጽናት ተምሳሌትነቷን አሳይታለች። ፍልቅልቋ ኮከብ በቅርቡ ሩት የተባለችዋን ሁለተኛ ልጇን መገላገሏንም ገልጻለች። በዚህም ክብደት ጨምራለች። ይሁን እንጂ ክብደቷን ቀንሳ ወደ አሸናፊነት እንደምትመለስ ተስፋዋ ጽኑ መሆኑን ትናገራለች።

ለደራርቱ ከእናትነት ኀላፊነት ጋር ታግሎ ማሸነፍ አዲስ አይደለም። በሲድኒ ኦሎምፒክ በርካቶች ከእናትነት ወደ አሸናፊ አትሌትነት መመለስ ይከብዳታል ቢሏትም፣ የደራርቱ ውጤት ግን ግምቶች ሁሉ ከንቱ ሆነው እንዲቀሩ አድርጓል። ባርሴሎና ላይ የበራችው ኮከብ ላለፉት ሀያ አመታት ተገልጾ የማያልቅ የድል ትንታኔን ገልጻለች። ከብዙ በጥቂቱ





ከግብጽ የመላ አፍሪካ ጨዋታዎች እስከ አቴንስ ግሪክ ደራርቱ በወርቅ፣ በብርና በነሐስ ሜዳሊያዎች ያልተንቈጠቈጠችበት የስኬት መሥመር የለም።

ቀዳሚዋ ኮከብ በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ የበርካታ ኮከቦችን የድል መንገድ ጠርጋለች። በአሳለፍነው ሺ ዓመት መገባደጃዎቹ ውስጥ በርትታ በሚቀጥለው ሺ ዓመት መጀመሪያዎቹ ውስጥ ሊንቦገቦጉ የሚችሉ ተተኪ ኮከቦችን ፈጥራለች። ፍልቅልቋ አትሌት፣ ቀድማ የበራች ኮከብ፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ እናት ደራርቱ ቱሉ።

ደራርቱ በ2000 በቤጅንግ ለሚካሔደው 29ነኛው ኦሎምፒክ ውድድር በመወዳደር ሜዳሊያዋን ይዛ ብትመጣ ምኞታችን ታሪካዊ እውነት ላይ የተመሠረተ እንጂ ባዶ ምኞት አይሆንም። ለደራርቱ ግን በሕይወቷ ዋነኛ ብላ የምትቆጥረውን ድል ለሃይማኖቷ መስጠት ትልቁ ቁም ነገር ነው። ስለዚህ ይህንን ሜዳሊያ ይዛ ብትመጣ በእምነቷ መሠረት፣ እንደ ሌሎቹ ሜዳሊያዎቿ ሁሉ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትሰጣለች። ይህች ሴት ጀግናና፣ ጨዋ፣ ሳቂታ፣ ስለ ሌሎች በጎ ተናጋሪ፣ ብቻ ሳትሆን እግዚአብሔርንም የምታከብር ናት።

## መወድስ

**የኢትዮጵያ አትሌት ነብር ነሽ ግሥላ**
**ደራርቱ የቀደምሽ ዓለምን በሞላ**
**እግረ ቀጭን ነሽ ልክ እንደ ሰሟ**
**ልበ ሙሉዋ ደግሞ እንደ አንበሳ**
**ፍቅርሽ ለአገርሽ ለወገኖሽ**
**በእንባ ተጻፈ በየጉንጮሽ**
**አሁንም ሳቂ በልጠሽ ድመቂ**
**ከታሪካችን እንዳትፋቂ**



## ትምህርተ ውልብታ

### ለቤተ ሰብ ፈቃድ የሰጠችው ሥፍራና አክብሮት

### ቀጣይነት ያለው ውጤታማነት ባለቤት ለመሆን ውድቀቶች ላይ ሳይሆን ድሎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ በጽናት መጓዝ የድል ባለቤት ያደርጋል

| ተ.ቊ | ዘመን /እ.ኤ.አ/ | የውድድሩ ስያሜ | ርቀት | አገር | የሜዳሊያ ዓይነት | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 1991 | የመላ አፍሪካ | 10.000 ሜ | ግብጽ ካይሮ | ወርቅ | |
| 2 | 1992 | የቢጋ ኦሎምፒክ | 10.000 ሜ | ስፔን ባርሴሎና | ወርቅ | በአፍሪካዊት ሴት የመጀመሪያው የወርቅ ሜዳሊያ |
| 3 | 1992 | አይ.ኤ.ኤፍ | 10.000 ሜ | ሀቫና ኩባ ወርቅ | | |
| | | የዓለም ዋንጫ | | | | |
| 4<br>5 | 1992<br>1995 | የዓለም አገር | 3.000 ሜ<br>ረጅም ርቀት | ሀቫና ኩባ ወርቅ<br>እንግሊዝ ዱርሃም | ወርቅ | ወደ እንግሊዝ ይበር የነበረው አውሮፕላን በአቴንስ ከተማ በመዘግየቱ ወደ ውድድሩ ሥፍራ ለመሄድ የ8 ሰዓት የአውቶቡስ ጉዞ ግድ ሆኖባት ነበር |
| 6 | 1995 | የዓለም ሻምፒዮን | 10.000ሜ | ጉተንበርግ ስዊድን | ብር | |
| 7 | 1997 | የዓለም አገር አቋራጭ ሻምፒዮን | ረጅም ርቀት | ጣሊያን ቱሪን | ወርቅ | |
| 8 | 2000 | የቢጋ ኦሎምፒክ | 10.000ሜ | አውስትራሊያ ሲድኒ | ወርቅ | |
| 9 | 2000 | የዓለም አገር አቋራጭ ሻምፒዮን | ረጅም ርቀት | ፖርቱጋል ቪላሞራ | ወርቅ | |
| 10 | 2001 | የዓለም ሻምፒዮን | 10.000 ሜ | ካናዳ ኤድመንተን | ወርቅ | |
| 11 | 2001 | ቶኪዮ የሴቶች | ማራቶን | ቶኪዮ ጃፓን | አሸናፊ | |
| 12 | 2001 | የለንደን ማራቶን | | እንግሊዝለንደን | የማራቶን አሸናፊ | |
| 13 | 2004 | የቢጋ ኦሎምፒክ | 10.000 ሜ | ግሪክ አቴንስ | ነሐስ | |



## የውልብታ ምንጭ


ሕይወትን የለወጡ እግሮች የኢትዮጵያ ሴት አትሌቶች አስደናቂ የሕይወት ታሪክ በተባበሩት መንግስታት የሥነ ሕዝብ ፈንድ የተዘጋጀ 1998 አዲስ አበባ ።

የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ታሪክ፣ በኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ የተዘጋጀ 1997 ዓ.ም. አዲስ አበባ ።

*The New York Times* July 3, 1996 *Tulu Running for Herself and Millions of Sisters*

*Runner's World Marathon New York City*

*Selamta: The in-flight Magazine of Ethiopian Airlines, Vol 24 Number 3, July – September 2007*

http://www/iaaf. org

http://www. wikepedia the free encyclopedia, Profile of Derartu Tullu

ቃለ ምልልስ፣ ከአትሌት ደራርቱ ቱሉ ጋር አዲስ አበባ ስታዲየም መጋቢት 15,1999 ዓ.ም.

## የአንባቢው የግል ማስታወሻ





## የውልብታ ምንጮች

### በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍት ጋዜጦችና ጆርናሌዎች


Aren, Gustav *Envoys of the Gospel in Ethiopia.* Stockholm, 1999

______ *Evangelical pioneers in Ethiopia.* Origins of the Evan gelical church Mekane Yesus. Stockholm & Addis Ababa, 1978

Aud sæveras, *In the Fiery Furnace*, Lunde publishers, (Trans lated by Harry T. Cleven,), Oslo, 1995

Bahiru Zewde *Pioneers of Change in Ethiopia:* the Reformist Intel lectuals of the Early Twentieth Century, Eastern African Studies, Addis Ababa University Addis Ababa, 2005

______ *A History of modern Ethiopia 1855 - 1974.*London, Athens & Addis Ababa, 1991

Berhanu Abebe, *The faith of forefathers Ethiopian text Teachings of Member Kifle Giorgis, put together byAleka Kidane Wold Kifle, compiled by his disciple Desta Tekle Wold with an introduction on the lives and works of these three scholars*

Cowley, Roger *A Geez Prologue Concerning the Work of Mamher Kefle Giyorgis on the Text andInterpretation of the Book of Ezekiel,* in Ethiopic Studies. Dedicated to Wolf Leslau on the Occasion of his Seventy-fifth birthday, November 14, 1981. Edited by Stanislav Segert and Andras Bodrog ligeti (Wiesbaden: Otto Harrassowitz, 1983)

Cameroon Tribune, N 3950-SAMEDI 22 AOUT. 1987

Christopher Clapham *Imperial Leadership in Ethiopia, African Aff airs*, Vol. 68, No. 271 (Apr., 1969), pp. 110-120 this ar ticle consists of 11 page(s).

Confederation Africaine de Football (CAF) 1957-199. Published to celebrate its 40th year anniversary. (1997)

Dietrich Bonhoeffer, *Public opposition to the Nazi*, Online Ex hibitions, *Ethiopian Pastor Speaks on Apartheid*, The Ethiopian Herald, Vol XXIX, No. 366, Tuesday, March 4, 1972.

Donald N. Levine Remarks on *the Occasion of the Award of Hon orary Doctorate to himself, by Addis Ababa University*, July 24, 2004

Eide, Øyvind M. *Revolution and Religion in Ethiopia*, Upp sala University,1996

Fikre Tolossa, *" Ashenafi Kebede: A composer with soul,* Ethiopian Review May, 1993.

Getachew Hayle, Aasulv Land, Samuel Rubenson (eds.) *The Missionary Factor in Ethiopia.* Papersfrom a Symposium on the Impact of European Missions on Ethiopian Society, Lund University, August 1996

Gudina Tumsa Foundation, *Witness and Discipleship, Leader ship of the Church in Multi-Ethnic Ethiopian in a time of Revolution*, The essential writings of Gudina Tumsa General Secretary of Ethiopia Evangelical Church Mekane Yesus (1929-1979) Addis Ababa.

*The life and ministry of Rev. Gudina Tumsa*, General Secretary of the Ethiopian Evangelical Church Mekane Yesus (EECMY), Addis Ababa, 2003.



Habtamu Bula, *"The Church should be a voice of the voice less"*, A short Biography of The Reverened Gudina Tumsa, Mekane Yesus Seminary, Addis Ababa, 1995

Jember Tefera, *"Entering the world of poverty"* A Doctoral Thesis for the partial completion of Doctor of Ministry Pro gram

Kimberlin, Cynthia Tsekimberlin, *" The scholarship and art of Ashenafi kebede (1938-1998)"*, Etnomusicology 43,2, 1999, 322-34

Kimberlin, Cyntain in Ashenafi Kebede, *Enyclopedia Aethiopica*, Harrassowitz verlog

Leslau, Wolf, *Comparative Dictionary of Geez (Geez-English and Eng lish-Geez)*, Wiesbaden: Otto Harrassowitz, 1987.

_____, *Concise Dictionary of Geez*, Wiesbaden: Otto Harrassowitz, 1989.

Molvaer, Reidulf K., *Black Lions: The Creative Lives of Modern Ethiopia's Literary Giants and Pioneers*, Lawrenceville: The Red Sea Press, Inc., 1997.

Onesimos Nesib, *The Oromo Spelling Book* Monkullo, 1894

Prouty, Chris *Empress Taytu and Menilek II*, Ethiopia, 1883-1910.London, 1996.

R Greenfield, *Ethiopia*, London 1965 p 372-373

Reuidlf Knut Molvaer "*Dabbaba Seifu*" in Encyclopedia Aethooica Vol 2 P.4

_________ *"Afewerq Yohannis and Debbebe Seifu, Notes on Ethiopian Writers of the late Twentieth century* " Northeast African Studies 6,3 1999

Shiferaw Bekele, *Gabra Heywat Baykedagn and the Emergence of a Modern Intellectual Discourse,* Sociology, Ethnology Bul letine, Vol. 1, No 3 February 1994

Tadele Yidnekackew Tessema In the world and in the world of sport. United publishers (1981) Addis Ababa

Tadesse Adera and Ali Jimale Ahmed, (Eds) *Silence is not Golden: a critical anthology of Ethiopian Literature,* (Biodun Jeyifo, Art and Ideology in the Plays of Tsegaye Gebre-Med hin) The Red Sea Press Inc., 1995

Terfasa Diga, *Onesimos Nesib, A Short Biography of Onesimos Nesib 1850 – 1931,* Addis Abab 1999

Tesgara Hirphoo, *Abba Gamachiis, Oneesimos Nasimos Nasib,* Hermannsburg, Amajjii 1999

Ullendorff, Edward, *The Ethiopians: An Introduction to the Country and People,* London: Oxford University Press, 1960

*Mekuria Bulcha Onesimos Nesib's Pioneering Contributions to Oromo Writing, University of Uppsala, Sweden, in Nordic Journal of African Studies 4(1): 36 – 59 (1995)*

Dirshaye Menberu *Onesimus Nesib c. 1856 to 1931 Ethiopian Evangelical Church Mekane Yesus (EECMY) Ethiopia*

*Aster Ganno, Encyclopaedia Aethiopica, vol. 1, edited by Siegbert Uhlig, pp. 387,388. Wiesbaden: Harrassowitz.*

Wikepedia the Free Encyclopedia, Profile of Solomon Tessema

Wikepedia the Free Encyclopedia, Profile of Derartu Tullu

*The New York Times* July 3, 1996 *Tulu Running for Herself and Mil lions of Sisters Runner's World Marathon New York City*



*Selamta: The in-flight Magazine of Ethiopian Airlines, Vol 24 Number 3, July – September 2007*

**በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍት**

አሸብር ገብረ ሕይወት የንግሥት አዜብ ታሪካዊ ጉዞ 1951ዓ.ም.

አለማየሁ አበበ (ካፕቴን)1997 *ህይወቴ በምድርና በአየር*

በዓሉ ግርማ *የቀይ ኮከብ ጥሪ* 1972 ዓ. ም.

በዓሉ ግርማ *ኦሮማይ* 1984 ዓ.ም.

በዓሉ ግርማ ከአድማስ ባሻገር

ባሕሩ ዘውዴ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966* ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ 1989 ዓ.ም.

ብርሃነ መስቀል ደጀኔና ጌታሁን ሽብሩ ከ፲፱ እስከ ፳፻ ድርሰት ያሥርቱ ምእት የብርዕ ምርት ክፍል ፩ ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፺፱

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፣*አፄ ሚኒልክ እና ኢትዮጵያ* ፣ብርሃን ይሁን፣አሥመራ፣1912

______*መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር* 1916 ንግድ ማተሚያ ቤት

ጌታቸው በለጠ፤ ኤሎሄ እና ሃሌሉያ፣ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (ቅጽ ሦስት1966 1992)፣ሚያዝያ 1992፣አዲስ አበባ

ደስታ ተክለ ወልድ፣ ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት (አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962)።

ዳዊት ገብሩ (ኮሎኔል)፣ ከንቲባ ገብሩ ደስታ የኢትዮጵያ ቅርስ ፣ አዲስ አበባ፣1985

ፊቃዱ ጉርሜሳ ኩሳ፣ የወንጌል እምነት እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ፣ አዲስ አበባ፣ጃኑዋሪ 1999 ዓ.ም

ኅሩይ ወ/ሥላሴ፣የሕይወት ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣1951

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ (አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948)።

______, ሃይማኖተ አበው ቀደምት።

መኮንን በሪ ( ካፕቴን ) 1995 አቪየሽን በኢትዮጵያ_

ይድነቃቸው ተሰማ ፣ሕዝብና አስተዳደር፣ ሞራል፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1954 ዓ ም አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ 1967

ታዬ ታደሰ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ሙዚየም፣ አንዳንድ የታወቁ የኢትዮጵያ ሠዓሊዎች አጭር የሕይወት ታሪክ 1962 እስከ 1950 ዓ.ም. ዩናይትድ ፕሬስ አዲስ አበባ 1977 ዓ.ም.

የሴቶች ክዋኔና ርእይ 1993 የኢትዮጵያ ሴቶች እንቅስቃሴ በ20ኛ ክፍለ ዘመን ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ንኡስ ጉዳይ ዘርፍ



ፋንታሁን እንግዳ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደር ጎልተው የወጡ ፖለቲካዊ ችግሮችና ትግሎች በቅርብ ባለሟላቸው የሕይወት ታሪክ መነሻነት ሲገመገሙ አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 1997 ዓ ም

ይሁን ዓለም ሰገድ "ፋና ወጊ" ነሐሴ ወር 1984 ዓ.ም.

ቃለ ክርስቶስ ዓባይ ኮሎኔል፣ "የ1953 የመንግሥት ግልበጣ ሙከራና ከ1908-1966 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ሂደት" 1997 ዓ.ም.

ኃይለ ገዮርጊስ ወርቅነህ ኢንጅነር ዶክተር የሕይወቴ ታሪክ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት 1992 ዓ.ም አዲስ አበባ

ለሮን ቤኔት ጁኒየር፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር፣ የሕይወት ታሪክ፣ ታምሩ ፈይሳና ዶ/ር አያሌው ቀኖ እንደ ተረጐሙት፣ 1964 ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ

ሕይወትን የለወጡ እግሮች የኢትዮጵያ ሴት አትሌቶች አስደናቂ የሕይወት ታሪክ በተባበሩት መንግስታት የሥነ ሕዝብ ፈንድ የተዘጋጀ 1998 አዲስ አበባ ።

የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ታሪክ፣ በኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ የተዘጋጀ 1997 ዓ.ም. አዲስ አበባ ።

ጸጋዬ ገብረ መድኅን እሳት ወይ አበባ መጽሐፍ 1999 የጀርባ ሽፋን

ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ የአናብስት ምድር፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት የታሪክ ዘገባ ከ1927 እስከ 1983 ዓ.ም. ሮም ማተሚያ ድርጅት 1999 ዓ.ም.

## ቃለ ምልልሶች

ከአቶ አለ ፊለገ ሰላም ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ሚያዚያ 1999

ከአባባ ተስፋዬ ሳህሉ ኤጀርሳ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ፣ የካቲት 1999 ዓ.ም።

ከጋዜጠኛ ማዕረጉ በዛብህ ጋር ግንቦት 14 ቀን 99 ዓ.ም. የተደረገ ቃለ ምልልስ።

ከአቶ ሙሉጌታ በሪሁን (የሕግ አማካሪና ጠበቃ) ጋር ረቡዕ ግንቦት 15 ቀን 1999 ዓ.ም. የተካሄደ ቃለ ምልልስ።

ከጋዜጠኛ ጉርፍነህ ይመር ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ፣ አዲስ አበባ ስታዲየም የካቲት 15 ቀን 1999

የአንጋፋ ጋዜጠኞች ስለ ጋዜጠኛ ሰሎሞን ተሰማ የሰጡት አስተያየትና ቃለ ምልልስ (1993-1994)

አቶ አስፋው ዳምጤ ቃለ መጠይቅ የካቲት 26 1999

ቃለ መጠይቅ ከአቶ አስፋው ዳምጤ ጋር መጋቢት 3,1999

ቃለ መጠይቅ ከዓለሙ ገብረ አብ ጋር የካቲት 1999

በየካቲት 1998 በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ዝክረ ጸጋዬ ገብረ መድኅን ዝግጅት ላይ አቶ አስፋ ወርቁ የተናገሩት

ቃለ ምልልስ ከደራሲና ጋዜጠኛ አንዳርጌ መስፍን ጋር የተካሄደ መጋቢት 6 ቀን 1999 ዓ.ም.

ቃለ ምልልስ ከጋዜጠኛ ይሙኑ ይርዳው ጋር የተደረገ የካቲት 21 ቀን 1999 ዓ.ም.



ቃለ ምልልስ ከደራሲ ማሞ ውድነህ ጋር አርብ የካቲት 23 ቀን 1999 ዓ.ም.

ከዶክተር ጀምበር ተፈራ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ሚያዚያ 1999 ዓ.ም

ከወ/ሮ ዘነበወርቅ ብሥራት ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ሚያዚያ 1999 ዓ.ም

ከወ/ሮ ሐረገወይን ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ሚያዚያ 1999 ዓ.ም

ቃለ ምልልስ፣ ከአትሌት ደራርቱ ቱሉ ጋር አዲስ አበባ ስታዲየም መጋቢት 15,1999 ዓ.ም.

ቃለ ምልልስ ከአትሌት ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ ጋር የተደረገ የካቲት 1999 ዓ.ም.

ቃለ ምልልስ ከአትሌት ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ ልጅ ከአቶ ጃገማ ዋሚ ጋር የተደረገ የካቲት 1999 ዓ.ም.

ቃለ ምልልስ ከአትሌት ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ ጉረቤት ጋር የተደረገ

ቃለ ምልልስ ከዶክተር ተስፋ ወርቅነህ ጋር ጳጉሜ 2 ቀን 1997 ዓ ም

ቃለ ምልልስ ከመምሬ ስለሺ ወልደ ሚካኤል ጋር መስከረም 27 ቀን 1998 ዓ ም

ቃለ ምልልስ ከአባ ጸጋዬ ቀነኒ ጋር የካቲት 30 ቀን 1999 ዓ ም

ቃለ ምልልስ ከዶክተር ደበላ ብሪ ጋር የካቲት 22 ቀን 1999 ዓ ም

## መጽሔቶችና ጋዜጣዎች

የካቲት መጽሔት 11ኛ ዓመት ቍጥር 5/1980 እሸቱ ከጃንሜዳ፣«በምድር ይድነቃቸው»

ከትምህርት ዓለም፣ ቅጽ 11 ቁ 1 መስከረም 1982 ዓ. ም. «ትምህርትና ስፖርት» ይድነቃቸው ተሰማ (ክፍል ሁለት)

ጦማር መስከረም 28 ቀን 1995 ዓ.ም.

ኔሽን (ኪነ ጥበብ) ታኅሣሥ 24 ቀን 1996 ዓ.ም.

ሩሕ ሐምሌ 12 ቀን 1994 ዓ.ም.

አዲስ ዘመን ጋዜጣ የካቲት 1971 ዓ. ም.

የካቲት መጽሔት፣ ከኀይሉ ጸጋዬ፣ "እንጋፋው ከያኒ"፣ ጥር፣ 1979 ዓ.ም፤ ገጽ 19 - 20

ማለዳ መጽሔት፣ "የተረት አባት አባባ ተስፋዬ"፣ የጹሑፊው ስም ያልተጠቀሰ፣ ቅጽ 2፣ ቍጥር 7 ጥርና የካቲት 1999 ዓ.ም፤ ገጽ 7-8 9

ማለዳ መጽሔት መጋቢት 1985 ዓ.ም. ቍጥር 3

ጦቢያ መጽሔት ጥቅምት 1989 ዓ.ም.

ብርሃን መጽሔት 1994 ዓ.ም.

መስከረም ቅጽ 1፣ 3 ፣1973 ዓ.ም.

ሩህ ቅጽ 2 1985 ዓ.ም.

ሰንደቅ 2ኛ ዓመት ቍጥር 77 1999 ዓ.ም.

መዝናኛ 1ኛ ዓመት ቍጥር 043 መጋቢት 25 ቀን 1997 ዓ.ም.



ኅሊና መጽሔት ነሐሴ 1984 ገጽ 8

ኢትእጽ ጋዜጣ ሐምሌ 1997 ገጽ 13

ጦቢያ መጽሔት የካቲት 1997 ገጽ 8

ለዛ መጽሔት ቁ 2 መስከረም 1985 ገጽ 8- 13

ሕሊና መጽሔት ነሐሴ 1984 ገጽ 6

ሙያችን መጽሔት 1999 ገጽ 36

ፀደይ መጽሔት ህዳር ወር 1989 ዓ.ም.

ኢንፎቴይመንት መጽሔት ጥቅምት ወር 1997 ዓ.ም.

ፈርጥ መጽሔት መሠረት አታላይ ደበበ ሰይፉ፣ ለኪነ ጥበብ ተፈጥሮ ለኪነ ጥበብ የሞተ ሐምሌ 1992 ዓ.ም.

ፈርጥ መጽሔት ገጣሚ ደበበ ሰይፉ እንዴት ኖሮ ሞተ? ግንቦት 1993 ዓ.ም.

Ethio air star ,1996 No-2 Golden Jubilee issue

Alpha-Ethiopia, sky lions(1996)airline pilots association

The Kansas city star July,19 1964

International Newsletter May 1986

## ቴሌቪዥንና ሬድዮ

ኤፍ.ኤም ሬድዮ የቅዳሜ ጨዋታ ዝግጅት ከሐያሲ እና ደራሲ አስፋው ዳምጤ ጋር የተደረገ ቆይታ፤ ታህሳስ 14 ቀን 1999 ዓ.ም.

የይድነቃቸው ተሰማን ህይወት አስመልክተው በቴሌቪዥን የተላለፉ የታዋቂ ግለሰቦች አስተያየቶች 1993 ዓ.ም. ።

ዐውደ ሰብ የቴሌቪዥን ፕሮግራም አስፋው ፊቃደ፣ «ያልተሸለመው ጀግኖ» ጋዜጠኛውን አስመልክቶ የተሰራ ፕሮግራም፣ 1994

## <u>ድረ ገጾች</u>

*http: www. Ethio sports. Com* /Ydnekachew. html smart, 2007
*http:// www. CAF online. org.*

*www.ethiopians.com* Negussay Ayele (Professor) /**tsegaye**/

*http://www/iaaf. org*

*http://www.* wikepedia the free encyclopedia, Solomon Tesema

*www. ethiomirror.com.* Ababa Tesfay`s Great Journey,

*www.fsu.edu*/fstime/FSTimes/Volume4/aug98 Dale A. Olsen,
*<u>http://en.wikipedia.org/wiki/Aster_Ganno</u>*

http://www/iaaf. org

## <u>ጥናታዊ ጽሑፎች</u>

Mestawet Aragaw, *The Hidden Talented Female Ethiopian Pianist*, senior thesis, Aug. 2006,

ተክቶ ታደሰ የደራሲ ደበበ ሰይፉ ሕይወት ታሪክና የሥነ ጽሑፍ ሥራው ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ /የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል 1993 ዓ.ም.



ኃይሉ ከበደ፣ የአለቃ ታዬ ገ/ማርያም የሕይወት ታሪክ፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ፣1963

ጥጋቤ አስረስ የነጋድራስ ገብረ ሕይወት ዐጭር የሕይወት ታሪክ ፣ በቀ.ኃ.ሥ. ዩኒቨርስቲ የድግሪ ማሟያ ጽሑፍ 1962 ዓ. ም.

«ሰሎሞን ተሰማ»፣ በጋዜጠኛው የሕይወት ታሪክ ዙሪያ የተሰናዳ ያልታተመ ጽሑፍ፣ 1994

በእንግሊዝኛ ቋንቋ ስለ አትሌት ዋሚ የተጻፈ አጭር የሕይወት ታሪክ...

በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ የዋሚ ቢራቱን ማንነት ጠቋሚ አጭር ትረካ